አፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 066 ኅዳር 6 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




# የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ተግዳሮቶችና መፍትሔዎች

ታደሠ ብናልፈው

**ዜና ትንታኔ**

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚገኘውን ምርት ለማሳደግ፤ ከውጪ የሚገቡ 90 ምርቶችን በሀገር ውስጥ ተክቶ ለማምረት ንቅናቄ ተፈጥሮ እየተሰራ ነው። ሆኖም በዘርፉ በርካታ ማነቆዎች እየተስተዋሉ ነው።

አንድ የመካከለኛ ኢንዱስትሪ አንቀሳቃሽ ወደ ምርት ለመግባት በቀላሉ ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ጊዜ እንደሚፈጅበት ይነገራል። በኢንዱስትሪው ያሉ ማነቆዎች ውስብስብ በመሆናቸው የዘርፉ ተዋንያን ከማምረት ይልቅ ወደ አገልግሎት መግባትን ይመርጣሉ። በኢንዱስትሪው የሚታዩ የፋይናንስ፤ የመሰረተ ልማት፤ የማምረቻ ቦታ እጥረት፤ የሰለጠነ የኃይል አቅርቦት ካልተፈታ ምርትና

የአምራች ኢንዱስትሪው... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ

## ኢትዮጵያ 20ኛውን የሥራ ድርጅት ጉባዔ ታስተናግዳለች

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በተያዘው ዓመት ግንቦት ወር ላይ 20ኛውን አህጉር አቀፍ ሥራ ድርጅት ጉባዔ እንደምታስተናግድ ተገለጸ።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የሚያዘጋጀው 20ኛው የሥራ ድርጅት ጉባኤ ከግንቦት 11 እስከ 15 ቀን 2017 ዓ.ም የአፍሪካ መዲና እና የብልጽግና ማሳያ እየሆነች በመጣችው አዲስ አበባ ይካሄዳል።

ኢትዮጵያ 20ኛውን... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አምባሳደር ፍጹም አረጋ

## የኢትዮጵያን ዳያስፖራ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን የሚያስጠብቅ የፖሊሲ ማሻሻያ ሊደረግ ነው

- በሩብ ዓመቱ ከሬሚታንስ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ተገኘ

ገጽ 2

# የነፃ አገልግሎቱ ተደራሽነት

ነፃነት አሰሙ

**ዜና ሐተታ**

መስከረም(ስሟ የተቀየረ) ትባላለች ደቡብ ወሎ ውስጥ ከሚገኝ ገጠራማ ስፍራ ከመጣች ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ እንደሆናት ትገልፃለች። አካባቢው አሁንም ድረስ ያለእድሜ ጋብቻ የሚፈፀምበት በመሆኑ እርሷም በአስራ ሰባት ዓመቷ ትምህርቷን አቋርጣ ተድራ እንደነበር ትጠቅሳለች። ነገር ግን ያገባት ሰው በእድሜ ከእርሷ ብዙም ያልራቀና ብስለት የሌለው በመሆኑ እንዲሁም በመጠጥ ሱስ ተገፋፍቶ የተለያዩ ጥቃቶችን ያደርስባት ስለነበር በወቅቱ ከወላጅ እናቷ ጋር በመመካከር ልጅ ላለመውለድ እንደወሰነች ትናገራለች።

ስለሆነም ለሶስት ወር የሚያገለግለውን መርፌ በአካባቢዋ ወደሚገኝ ጤና ጣቢያ እየሄደች በየጊዜው ትወጋ እንደነበር አስታውሳ፤ ለዚህ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ ስልሳ ብር ከዛ በኋላ ደግሞ ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር የቆየ ትዳሯን ፈትታ ወደ አዲስ አበባ እስከመጣችበት ጊዜ ደግሞ አንድ መቶ ብር እየከፈለች አገልግሎቱን ስታገኝ እንደነበር ትገልፃለች። አገልግሎቱን ካገኘች በኋላም መከላከያው ከመቼ እስከመቼ እንደሚያገለግል ከሚገልፅ ወረቀት ውጪ ምንም አይነት ደረሰኝ እንደማትቀበል ታስረዳለች።

በጤና ሚኒስቴር የእናቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች



ጤና ዘርፍ የቤተሰብ እቅድ ከፍተኛ ባለሙያ የሆኑት ወይዘሮ ገነት ድረስ በበኩላቸው እንዲህ አይነት መረጃ እንደሌላቸው ገልጸው፤ ለአገልግሎቱ ክፍያ የሚቀበል የጤና ተቋም ካለ ግን እንደሚቀጣ ይገልፃሉ። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከክልል ወደ ዞን ከዞን ወደ ወረዳ እያለ በአገልግሎቱ ዙሪያ ያሉ ጉዳዮች ላይ ክትትል የሚያደርጉ ባለሙያዎች እንዳሉትም ያስረዳሉ።

መድኃኒቱ በነፃ እስከቀረበ ድረስ የሚሸጥበት ምክንያት የለም የሚሉት ባለሙያዋ፤ የዚህ አይነቱ አሰራር ሪፖርት ካለ ግን እርምጃ እንደሚወሰድበት ይገልፃሉ። መንግሥት ለእነዚህ መድኃኒቶች በዓመት እስከ አርባ ሚሊዮን ዶላር እንደሚያወጣም ጠቁመዋል። በመድኃኒት አቅርቦቱ ላይ ይህን ያክል ገንዘብ ወጪ የሚደረገው አገልግሎቱን በነፃ ተደራሽ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነም ያብራራሉ።

የነፃ አገልግሎቱ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory




Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565



አምባሳደር ፍጹም አረጋ

## የኢትዮጵያን ዳያስፖራ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን የሚያስጠብቅ የፖሊሲ ማሻሻያ ሊደረግ ነው

### -በሩብ ዓመቱ ከሬሚታንስ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ተገኘ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ:- ዳያስፖራውን የሀብት ምንጭ ብቻ አድርጎ የመመልከት ሁኔታን በመሰረቱ የሚቀይር፣ በሀገሩ ጉዳይ የበለጠ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ በማድረግ ሚዛኑን የሚያስጠብቅ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ፖሊሲን ለማሻሻል እየሰራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ገለጸ።

በ2013 እ.አ.አ በወጣው የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ፖሊሲ ላይ በወሎ ዩኒቨርሲቲ መሪነት ጅማ፣ ጅግጅጋ እና ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲዎች ተሳታፊ ሆነው ባደረጉትት ጥናት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት ውይይት ተካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ፍጹም አረጋ እንዳሉት፤ ወቅቱን ባገናዘበ መልኩ የዳያስፖራውን ተጠቃሚነት ለማስፈን ፖሊሲውን ማሻሻል አስፈልጓል። በአሁኑ ጊዜም የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ፖሊሲን ለማሻሻል የመጨረሻ ምእራፍ ላይ ደርሷል፡፡

አሁን በስራ ላይ የሚገኘው ፖሊሲ ግዴታ የሚጥል መሆኑን በመጥቀስ፤ ፖሊሲው መብትን በሚያስጠብቅ መልኩ እንዲቃኝ በማድረግ ማሻሻያ እንደሚደረግበት ጠቁመዋል፡፡ ፖሊሲው ለዜጎች መብት የሚቆረቆር፣ ሚዛንን የሚያስጠብቅ መብትንም የሚያከብር ይደረጋል ብለዋል አምባሳደር ፍጹም፡፡

ፖሊሲው ሲጠና አናውቀውም የሚሉ የዘርፉ አካላት መኖራቸው፣ በኢኮኖሚ ዘርፍ የተደረገው ማሻሻያ፣ ዲጂታላይዜሽን መምጣቱ ፖሊሲውን ለማሻሻል ገፊ ምክንያት ከሆኑት መካከል እንደሚካተቱ አምባሳደር ፍጹም ጠቅሰዋል።

የተለያዩ ለውጦች መጥተዋል፤ በርካታ ኢትዮጵያ ውያን ዳያስፖራዎች በኢንቨስትመንት ዘርፍ ተሰማርተው ተጠቃሚ መሆናቸውን እና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን፣ በሀገራቸው በፖለቲካ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ንቁ ተሳትፎ ማድረ ጋቸውንም ጠቁመዋል፡፡

ወቅቱን በዋጀ መንገድ የዲጂታል ቴክኖሎጂ መምጣቱ፣ ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚ እየተደረገ ያለው ሽግግር እና ሰው ሰራሽ አስተውሎት በፖሊሲው ትግበራ ሂደት አዲስ ቅኝት ያመጡ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት ፖሊሲው እንዲሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በጥናቱ መለየቱንም ጠቁመዋል።

የጥናት ቡድኑ አባል ረዳት ፕሮፌሰር ሙሉጌታ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ ፖሊሲውን ማእከል በማድረግ በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን ጠቁመዋል፡፡ ሆኖም ፖሊሲው ሲዘጋጅ በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ እንጂ አሁናዊ አዝማሚያዎችን ያገናዘበ እንዳልነበረ ነው ያስታወሱት፡፡

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን፣ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች፣ አረንጓዴ ኢኮኖሚን ጨምሮ በየጊዜው ተግባራዊ የተደረጉ ኢኮኖሚያዊ እቅዶችን ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀ እንዳልነበረ እና በየወቅቱ ማሻሻያ የተደረገበት አለመሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ሰነዱ በዕድሜው መርዘም ምክንያት በየጊዜው እየወጡ ያሉትን ሀገራዊ እቅዶች አለማካተቱም በትግበራ ሂደት እንደክፍተት ማጋጠሙም ተነስቷል።

በሩብ ዓመቱ ከሬሚታንስ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን፣ በዚህ ሂደት ከቀጠለ በዓመቱ ስድስት ቢሊዮን ዶላር ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ፤ ነገር ግን ከዚህም በላይ ለማግኘት እንደሚሰራ አመልክተዋል፡፡

# አዲስ አበባ ከ30 በላይ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በስኬት በማስተናገድ የዲፕሎማሲ መዲናነቷን አስመስክራለች

## -ከሳዑዲ አረቢያ 94 ሺህ ዜጎች ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ:- አዲስ አበባ በሩብ ዓመቱ ከ30 በላይ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በስኬት በማስተናገድ የዲፕሎማሲ መዲናነቷን ማስመስከሯን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። በሳዑዲ አረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ 94 ሺህ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው መመለሳቸው ተገልጿል።



አምባሳደር ነቢያት ጌታቸው

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ነቢያት ጌታቸው ለመገናኛ ብዙኃን ትናንት በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ አዲስ አበባ ከ30 በላይ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በስኬት በማስተናገድ የዲፕሎማሲ መዲናነቷን አስመስክራለች።

ኢትዮጵያ በሩብ ዓመቱ በኮንፍረንስ ቱሪዝም እና ዲፕሎማሲ ዙሪያ በተሰሩ ሥራዎች የአፍሪካ ድምጽና ወኪል መሆኑዋን በተገቢው ደረጃ ማሳየት ችላለች ያሉት ቃል አቀባዩ፤ አዲስ አበባም የኮንፍረንስ ቱሪዝምንና ዲፕሎማሲን በመሳብ ረገድ አቅሟ እያደገ መምጣቱንና የዲፕሎማሲ መዲናነቷን ያስመሰከረችበት ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከ30 በላይ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በስኬት ማስተናገዷን ጠቅሰው፤ ከርሃብ ነፃ ዓለም ጉባኤ፣ የካፍ ጉባኤ፣ ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ፣ የአፍሪካ ንግድ ሚኒስትሮች ጉባኤና ሌሎች ጉባኤዎች መዘጋጀታቸውን ጠቅሰዋል።

ከረሃብ ነፃ ዓለም ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ እያከናወነች ያለችውን ሥራዎች በተሞክሮነት መቅረባቸውን ገልጸው፤ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን በስፋት ለጉባኤው ታዳሚዎች ማሳየት መቻሉን ተናግረዋል።

የጉባኤዎቹ በተሳካ ሁኔታ መካሄድ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ አቅምና ሚና ያሳየ መሆኑን በመግለጽ፤ ጉባኤዎቹ ከገጽታ ግንባታ የቱሪዝምን ገቢ ከማሳደግ አኳያና የተለያዩ ልምዶችን ለማጋራት ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው ጠቁመዋል።

ጉባኤዎቹ ኢትዮጵያ በሁሉም መስኮች እያደረገች ያለችውን የልማት እንቅስቃሴዎችን በተግባር ያሳየችበት መሆኑን የገለጹት አምባሳደር ነብያት፤ በተለይም “ከርሃብ ነፃ ዓለም” ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ የተሳተፉ የሀገራት መሪዎችና የተቋማት የሥራ ኃላፊዎች የኢትዮጵያን ዘርፈ ብዙ የልማትና የለውጥ ውጤቶችን ተመልክተዋል ብለዋል።

በሌላ በኩል በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ(ዶ/ር) የተመራው ልዑክ በሩሲያ ሶቺ በተካሄደው የሩሲያ-አፍሪካ አጋርነት የሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ተግባራትን ማከናወኑን ጠቅሰው፤ ከሩሲያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሴርጌ ላቭሮቭና ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት አቻዎቻቸው ጋር በሁለትዮሽ፣ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ስኬታማ ምክክር መደረጉን ተናግረዋል።

በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲም በቻይናዋ ጂያንሱ ግዛት ዋና ገዢ ሹ ኩሊን የተመራ የግዛቷ 15 ግዙፍ ኩባንያዎች፣ የሥራ ኃላፊዎች የሚሳተፉበት የንግድና ኢንቨስትመንት ፎረም በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ በመግለጽ፤ ፎረሙ የኢትዮ-ቻይናን በሁኔታዎች የማይለዋወጥ ስትራቴጂካዊ አጋርነት በንግድና ኢንቨስትመንት ይበልጥ ለማጠናከር አይነተኛ ፋይዳ እንዳለውም ገልጸዋል።

በተጨማሪም በዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ መንግሥት ከሚያዚያ 14 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 2017 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ በሳዑዲ አረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ 94 ሺህ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው መመለሳቸውን ገልጸው፤ ከማይናማር 31 በአስቸጋሪ ሁኔታ የነበሩ ዜጎች ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያውያን በሕገወጥ ደላሎች ከመታለልና የሥራ ስምሪት ስምምነት ሳይደረግ ከሚደረግ ጉዞ መቆጠብ እንደሚኖርባቸውም አስገንዝበዋል።

# እውቅናው ሴቶች በተሰማሩበት መስክ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ማሳያ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ:- የእውቅናና ሽልማት መርሃ ግብሩ ሴቶች በተሰማሩበት መስክ ምን ያህል ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ማሳያ ነው ሲል የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ በ2016 የትምህርት ዘመን ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ የዩኒቨርሲቲ ተመራቂና የ12ኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች እውቅና ሽልማት በትናንትናው እለት አበርክቷል።

በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የቢሮው ኃላፊ ወይዘሮ ወይንእሸት ዘሪሁን እንደገለጹት፤ የእውቅናና ሽልማት መርሃ ግብሩ ዋና ዓላማ ሴቶች በተሰማሩበት ዘርፍ ምን ያህል ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ለማሳየትና ታዳጊ ሴቶችም ከእነዚህ ውጤታማ ተማሪዎች ትምህርት እንዲወስዱ የሚያስችል ነው።

ቢሮው የሴቶችን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይሰራል። ከዚህ ውስጥ ዋነኛው የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ ነው ብለዋል።

ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመሆን ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ ያለውን የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ እንዲጨምር የተለያዩ ስራዎች እንደሚከናወኑም ገልጸዋል።



ወይዘሮ ዝናሽ ከተማ



ወይዘሮ ወይንእሸት ዘሪሁን

የሚከናወኑት ስራዎች ሴቷን ትምህርት ላይ ማሳተፍ ብቻም ሳይሆን ከወንዱ ጋር ተወዳድራ የተሻለ ውጤት ይዛ እንድትወጣም የሚያደርጋት መሆኑንም ተናግረዋል።

የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ረገድም ሴቶች ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ስራ ፈላጊ ብቻ ሳይሆኑ ስራ ፈጣሪ ሊሆኑ ይገባል ያሉት ወይዘሮ ወይንእሸት፤ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችም እንደ መልካም አጋጣሚ ወስደው በስራ ገበታቸው ላይ ውጤታማ መሆን ይኖርባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ የሴቶች ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ዝናሽ ከተማ በበኩላቸው፤ የእውቅና ሽልማቱ መርሃ ግብሩ ዘንድሮ ለሁለተኛ ጊዜ መካሄዱን ገልጿል።

ተመራቂ ተማሪዎች ጠንካራ ስራ ፈጣሪዎች በመሆን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ፤ በቀጣይ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የምትገቡ ተማሪዎችም ጠንክራችሁ በማጥናት ብቁ ዜጋ ለመሆን መጣር ይኖርባችኋል ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የእውቅናና ሽልማቱ ለ30 የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ላመጡ ሴት ተማሪዎችና ለ50 ሴት ተመራቂ ተማሪዎች ተበርክቷል።

# ብዝሃነትን ባከበረ መልኩ የሚገነባ ሀገራዊ መግባባት አንድነት ለማጠናከር ያግዛል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ብዝሃነትን ባከበረ መልኩ የሚገነባ ሀገራዊ መግባባት የሚፈለገውን ሀገራዊ አንድነት ለማጠናከር እንደሚያግዝ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ትግሉ መለሰ አስታወቁ።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ትግሉ መለሰ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፣ ብዝሃነትን ባከበረ መልኩ የሚገነባ ሀገራዊ መግባባት ጠንካራ አንድነት ለመፍጠር ያስችላል፡፡

ሀገራዊ አንድነት ብዝሃነትን ከግምት ባስገባና በጠበቀ ሁኔታ መከናወን አለበት ያሉት አቶ ትግሉ፤ እራስን ከማስተዳደር ጋር በተገናኘ የሚኖሩ ልዩ ፍላጎቶችንና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ የሚገነባ ሀገራዊ መግባባት የሚፈለገውን ጠንካራ ሀገራዊ አንድነት ለመፍጠር ትልቅ ሚና አለው ብለዋል።

የኢትዮጵያ የተለያዩ ባህሎች፣ እሴቶችና ሃይማኖቶች ያሏት በመሆኑ ብዝሃነትን ባማከለ መልኩ ሀገራዊ አንድነት ላይ መስራት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ትግሉ ገለጻ፣ ህብረብሄራዊነት የኢትዮጵያ ተጨባጭ እውነታ ነው። የፌዴሬሽን ምክር ቤት እውቅና የተሰጣቸው 76 ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አሉ። ሁሉም የራሳቸው ባህል፣ ማንነትና እራስን በራስ ማስተዳደርን ጨምሮ



ብዙ ፍላጎት አሏቸው፡፡ ሀገራዊ አንድነት በመፍጠር ሂደት ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶች ሊጠበቅ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

መድብለ ባህላዊና ህብረብሄራዊነት አንድ ላይ ተሳስረው መሄድ አለባቸው ያሉት አቶ ትግሉ፣ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፍላጎት ከሀገር አንድነት ጋር ሚዛንን አስጠብቆ ማስኬድ ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ጽህፈት ቤት ኃላፊው ማብራሪያ፣ ባለፉት ዓመታት በፌዴራሊዝም ሥርዓቱ ውስጥ ያጋጠሙ ችግሮች ብዝሃነት የተስተናገደበት መንገድ ሚዛኑን ጠብቆ ላለመሄዱ ማሳያ ነው። ችግሩን ለመፍታት አሁን ላይ ሀገራዊ አንድነት ላይ ያደላ ሥራ መሥራት እንደሚጠበቅ አመላካች ሁኔታዎች መታየታቸውም ጠቅሰዋል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት አንድነት፣ አብሮነትና ወንድማማችነትን ከማጎልበት አንጻር ግዴታና ስልጣን አለበት ያሉት የጽህፈት ቤት ኃላፊው፤ ይህንን ግዴታውንና ስልጣኑን እየተወጣ ነው ብለዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋሉ ግጭቶች ራሳቸውን የቻሉ ፖለቲካዊ አንድምታዎችና ከአስተዳደር ጋር የተገናኙ ጉዳዮች መገለጫዎች መሆናቸውን አመልክተው፤ ችግሮችን ለመፍታት ሀገራዊ መግባባት ላይ መሥራት አስፈላጊ እየሆነ የመጣበት ጊዜ መሆኑን ተናግረዋል።

የዘንድሮው 19ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን የሚከበረው "ሀገራዊ መግባባት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሃሳብ ነው። ይህ ደግሞ ለሀገራዊ አንድነት ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸዋል።

# “ከለውጡ ወዲህ የተጀመሩ የግብርና ሥራዎች በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ተጨባጭ ለውጥ እያመጡ ነው”

**- አቶ ጥላሁን ከበደ**
**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር**

**ሞገስ ጸጋዬ**

አርባ ምንጭ፡- ከለውጡ ወዲህ የተጀመሩ የግብርና ስራዎች በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ተጨባጭ ለውጥ እያመጡ መሆኑን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ አስታወቁ።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ ብዙ ጸጋና አቅም ቢኖራትም ለረጅም ጊዜ ከተረጂነትና ከኋላቀርነት መላቀቅ አልቻለችም። ከለውጡ ወዲህ ይህ ታሪክ እየተቀየረ ነው፤ እንደ ሀገር በኢኮኖሚው የታሪክ እጥፋት እየተመዘገበ ነው።

ከለውጡ በኋላ በሀገር ደረጃ የተጀመሩ የግብርና ስራዎች በተጨባጭ ኢኮኖሚው ላይ ለውጥ እያመጡ መሆኑን ገልጸው፤ የግብርና ስራን በእውቀትና በውጤታማ ፖሊሲ በመምራት፣ ጸጋዎችን በመለየትና ለስነምህዳሩ ተስማሚ የሆኑ ሰብሎችን በመዝራት በግብርናው ዘርፍ ተጨባጭ ለውጥ እየተመዘገበ ነው ብለዋል።

እንደ ሀገር በግብርናው ዘርፍ የመጣው ለውጥ በስንዴ ምርት የተመዘገበው ውጤት አንዱ ማሳያ ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ምርታማነትን የሚያሳድጉ ምርጥ ዘሮችን በመጠቀምና በዝናብ ጥገኛ ያልሆነ ግብርናን በማስፋፋት ኢኮኖሚው ላይ ውጤት ማምጣት ተችሏል ነው ያሉት።

በዚህም ከውጭ የሚገባውን የስንዴ ምርት በማስቀረት ወደ ውጭ መላክ የሚያስችል አቅም መፈጠሩን አውስተው፤ በዚህም የታሪክ እጥፋት ተመዝግቧል፣ በግብርና የተመዘገበውን በቱሪዝም ዘርፉም በመድገም ኢኮኖሚውን ይበልጥ የማሳደግ ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

የተመዘገበው የግብር ውጤት በዓለም አቀፍ ድርጅቶችና በሀገራት እውቅና የተሰጠው ነው ያሉት አቶ ጥላሁን፣ በሌማት ትሩፋት እየተሰራ ያለው ስራ ጥሩ ውጤት እያስመዘገበ ነው። ከለውጡ ወዲህ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ የተሰሩ ገበታ ለሸገር፣ ገበታ ለሀገርና ገበታ ለትውልድ የቱሪዝም መዳረሻዎች በአጭር ጊዜ አገልግሎት እየሰጡ ነው። የቱሪስት መዳረሻዎች ሀገር ያላትን አቅም



ፎቶ፡- ሃዲስ አብርሃ

ማሳያ ከመሆናቸውም በላይ ለኢኮኖሚው መነቃቃት ትልቅ ፋይዳ አላቸው ብለዋል።

ደቡብ ኢትዮጵያ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ እድገት የራሱን ሚና እየተጫወተ ነው ያሉት አቶ ጥላሁን፣ በተቋቋመ በአንድ ዓመት ውስጥ በርካታ የልማት ስራዎች አከናውኗል። ክልሉ ለሀገር ኢኮኖሚ ያለው አስተዋጽኦ እንዲጨምር በራስ አቅም ለኢንቨስትመንት ምቹ የማድረግ ስራ ስለመሰራቱ ጠቅሰዋል።

ከልማትና ከመልካም አስተዳደር አኳያ የሕዝብ ጥያቄዎችን የመፍታት ስራ እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ጥላሁን፣ በቡና፣ በአትክልትና በጥራጥሬ በርካታ ሀብት ያለው በመሆኑ ግብርናውን በልዩ ትኩረት የመደገፍ ስራ እየተሰራ ይገኛል ነው ያሉት።

ክልሉ ለኢንቨስትመንት ምቹ በመሆኑ በግሉ ዘርፍ ተመራጭ እየሆነ ነው፣ በዚህም ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር መቻሉን ገልጸው፤ በክልሉ ማልማት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ምቹ አቅም መኖሩን ገልጸው፤ ለማልማት ወደ ክልሉ ለሚመጡ ባለሀብቶች አስፈላጊው እገዛ ይደረጋል ብለዋል።

# በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት፡-

**- ስምንት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር የካሳ ክፍያ ግምት ተዘጋጅቷል**

**- ከሁለት ሺህ በላይ የግል ባለይዞታዎች ይነሳሉ**

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ስምንት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር የካሳ ክፍያ ግምት መዘጋጀቱን እና ከሁለት ሺህ በላይ የግል ባለይዞታዎች እንደሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር ዓባይ ገለጹ፡፡ የሚነሱ ዜጎች ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ሳይንገላቱ እንዲዛወሩ እየተደረገ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር ዓባይ ሁለተኛውን ዙር የኮሪደር ልማት አስመልክተው ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ከሁለት ሺህ 800 በላይ ሄክታር ስፋት እና 135 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የኮሪደር ልማት እየለማ ነው።

የኮሪደር ልማቱ የአስፋልት፣ የሳይክል እና የእግረኛ መንገዶችን፣ የወንዝ ዳር ልማትን፣ መዝናኛዎችን፣ የሕፃናት መጫወቻዎችን፣ የመኪና ማቆሚያዎችንና የእግረኛ ማቋረጫዎችን ያካተተ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ወደፊት የሚጨምር ቢሆንም እስካሁን በተደረገው ልየታ መሰረት በኮሪደር ልማቱ ሁለት ሺህ 074 የሚደርሱ የግል ይዞታዎች እንደሚነሱ ጠቁመው፤ እስካሁን ከ500 በላይ ለግል ባለይዞታ ተነሺዎች ተገቢው ካሳ መሰጠቱን ገልጸዋል።

ስምንት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር የካሳ ክፍያ ግምት ተሰርቶ፤ አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን አመልክተው፤ ለቀሪዎቹም ካሳ፣ ማጓጓዣ እና የቤት ኪራይ እና ሌሎች ክፍያዎችን ሳንፈጽም ከቦታቸው አናስነሳም ብለዋል፡፡

የልማት ተነሺዎች በሚሰፍሩባቸው አካባቢዎች ትምህርት ቤት፣ መንገድ፣ ውሃ፣ የጤና ተቋማት እና ሌሎች አስፈላጊ መሰረተ ልማቶችን የማሟላት ስራ እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል።

የኮሪደር ልማቱ ከመጀመሩ በፊት የልማት ተነሺዎች ምትክ ቤትና የካሳ ጉዳይ በትኩረት ሲሰራበት መቆየቱን ገልጸው፤ ስራው እንደተጀመረ የልማት ተነሺዎች ወደተዘጋጀላቸው ስፍራ ያለምንም መንገላታት እንዲዛወሩ እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ለግል ባለይዞታዎች ካሳ ከመክፈል በተጨማሪም ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ለሁለት ዓመት የሚሆን የቤት ኪራይ እና የማጓጓዣ ገንዘብ የካሳ ሕጉ በሚለው መሰረት እንደሚሰጣቸው አብራርተዋል፡፡

እንደ ምክትል ከንቲባው ገለጻ፤ በልማት ምክንያት ለሚነሱ የልማት ተነሺዎች የወቅቱን ገበያ መሰረት ያደረገ ዋጋ ተጠንቶ ለቤታቸው ግምት ይሰጣቸዋል፡፡ ቦታን በሚመለከት ግን ምትክ ስለሚሰጥ ግምት አይሰራለትም፡፡ ከቀበሌ ቤት ለሚነሱ የልማት ተነሺዎች ደግሞ ምትክ ቤት የሚሰጥ እና ማጓጓዣ የመክፈል ስራ እየተሰራ ስለመሆኑ አክለዋል፡፡

የሰነድ አልባ ባለይዞታዎችን በሚመለከት ባለው የሰነድ አልባ ሕግና መመሪያ መሰረት የሚስተናገዱ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሰነድ አልባ በሕገወጥ መንገድ የተገነባው ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰነድ አልባ የሚያስብሉ መመዘኛዎች መኖራቸውን ገልጸው፤ ሰነድ አልባ ለሆኑ የልማት ተነሺዎች ዘላቂ መብታቸውን የሚያረጋግጡበት ቦታ ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል ብለዋል፡፡

ሁለተኛውን ምዕራፍ የኮሪደር ልማት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በተሰራው ስራም የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን የማጠናቀቅ እንዲሁም ሳይቱን ነጻ የማድረግ፣ ተቋራጭ እና አማካሪ የመመደብ ስራ መከናወኑን ተናግረዋል፡፡

የኮሪደር ልማት በሚሰራባቸው አካባቢዎች ተቋማት በቅንጅት እንዲሰሩ እየተደረገ ስለመሆኑም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ሁለተኛው ዙር የኮሪደር ልማት ስራ 2 ሺህ 879 ሄክታር ስፋት፤ 135 ኪሎ ሜትር የኮሪደር ርዝመት ያለው ሲሆን፤ 240 ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ፣ 237 የእግረኛ መንገድ፣ 32 የሕፃናት መጫዎች ቦታዎች፣ 79 የሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች ፣ 114 የታክሲ እና አውቶቡስ መጫኛ እና ማውረጃን ያካተተ መሆኑም ተገልጿል።

58 የኤሌክትሪክ መኪና ቻርጅ ማድረጊያ ቦታዎች፣ 368 ሄክታር አረንጓዴ ልማት ሽፋን ያላቸው ቦታዎች፣ የ111 ኪሎ ሜትር ሳይክል መንገድ፣ 17 የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች፣ 106 የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች፣ 121 ኪሎ ሜትር የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር፣ 182 ኪሎ ሜትር የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር፣ 50 የተሽከርካሪና እግረኛ መተላለፊያ፣ 75 ኪሎ ሜትር የድጋፍ ግንብ (ሪቴይኒንግ) ስራዎችን የሚያካትት ነውም ተብሏል ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በቀጣናው ሰላም እና ልማትን ለማስፈን የሚረዳ አዲስ የትብብር ምዕራፍ!

የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ በግጭት አዙሪት ውስጥ አልፈዋል። አሁንም ከዚህ ችግር ሙሉ ለሙሉ አልተላቀቁም፡፡ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ያላቸውን ከማጣት እና ሕዝቦቻቸውን ለከፋ ችግር እና መከራ ከመዳረግ ያለፈ ያተረፉት አንዳች ነገር የለም። በድህነታቸው ላይ ድህነትን ፣ በኋላ ቀርነታቸው ላይ ኋላ ቀርነት በመጨመር ትናንቶችን ናፋቂ አድርጓቸዋል።

የነበሩ የቅኝ ግዛት አስተሳሰቦች የወለዷቸው የመለያየት ዝማሬዎች፤ አምባገነን መሪዎች የፈጠሯቸው የመስፋፋት እሳቤዎች፤ አካባቢው ካለው ጂኦ ፖለቲካዊ ጠቀሜታ አኳያ ስትራቴጂክ ጥቅም አለኝ የሚሉ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ... ወዘተ በአካባቢው ሰላም እና መረጋጋት እንዳይሰፍን ፈተና ሆኖ ቆይቷል።

በተለይም በየወቅቱ ወደ ስልጣን የሚመጡ የአካባቢው ሀገራት መንግሥታት የቀጣናውን ሕዝቦች የሰላም እና የልማት ፍላጎት ተረድተው፤ ለዚህ የሚሆን አካባቢዊ የትብብር ህብረት ፈጥረው ከመንቀሳቀስ ይልቅ፤ ከትናንት የተዛቡ ትርክቶች በመነሳት ልዩነቶችን አስፍቶ ወደ ግጭት የሚወስዱ መንገዶችን ሲከተሉ ቆይተዋል።

በዚህም አካባቢው ለረጅም ዓመታት ሰላም አጥቶ ቆይቷል፤ ከዚህም በከፋ መልኩ ዓለም አቀፍ የሽብርተኛ ቡድኖች እና ጽንፈኛ ኃይሎች መናኸሪያ ሆኗል። ችግሩ ከአካባቢው ሀገራት አልፎ ዓለም አቀፍ ስጋት የሆነበትም ሁኔታ ተፈጥሯል። ስጋቱን ለመቀልበስ የተደረጉ ጥረቶችም ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል።

በርግጥ የአካባቢው ሀገራት ካላቸው የተፈጥሮ ጸጋ እና ታሪካዊ የወንድማማችነት ጉርብትና አኳያ፤ ፍትሐዊ ለሆነ ተጠቃሚነት፣ አቅሞቻቸውን በጋራ አልምተው፤ ተጽእኖ ፈጣሪ አካባቢያዊ የኢኮኖሚ አቅም ሆነው የሚወጡበት ዕድል ከፍ ያለ እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ ይታመናል።

በተለይም የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ ጥሎት የሄደውን ፣ የመለያየት ትርክት እና ትርክቱ የፈጠረውን አለመተማመን በማስወገድ ፣ በአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች መካከል የነበረውን እና ያለውን ወንድማማችነት በማደስ ፣ አካባቢውን የተሻለ የልማት ኮሪደር ማድረግ ይቻላል።

የኢትዮጵያ መንግሥት አሁን ላይ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ሰላምን በመፍጠር ቀጣይነት ያለው አካባቢያዊ ልማት ለመፍጠር የሚያደርገው ጥረትም ይህንኑ እውነታ ታሳቢ ያደረገና ለአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች የሰላም እና የልማት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት የሚያስችል አዲስ የትብብር ምዕራፍ ነው።

በሕዝቦች መካከል አለመተማመንን በማስወገድ ፍትሐዊ እና ዘላቂ ተጠቃሚነት ላይ መሰረት ያደረገ ጉርብትና መፍጠር የሚያስችል፣ከሴራ እና ከመደነቃቀፍ ወጥቶ ፣በበጎ ህሊና ወደ መደጋገፍ፣ አብሮ ቆሞ ወደ መራመድ የሚወስድ ዘመኑን የሚዋጅ ፣ ከትናንት የሚያሻግር አስተሳሰብን መሰረት ያደረገም ነው።

ይህንን መልካም/ታሪካዊ አጋጣሚ በአግባቡ ተረድቶ ፤ ለአካባቢው ሕዝቦች የጋራ እጣ ፈንታ አብሮ ከመጓዝ ይልቅ፤ ማንንም አትራፊ ሊያደርጉ በማይችሉ የትናንት የጥፋት እሳቤዎች መነዳት የታሪክ ተጠያቂነትን ከማስከተል ባለፈ፤ በአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች የሰላም እና የልማት ፍላጎት በተቃርኖ መቆም ነው።

ዓለም ለትብብር እና ፍትሐዊ ለሆነ የጋራ ተጠቃሚነት ትልቅ ዋጋ ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ባለበት በዚህ ዘመን፤ የሀገር እና የሕዝብ ውክልና ይዞ የራስን የፖለቲካ ፍላጎት እና ፍላጎቱ የወለደውን ተጠቃሚነት እውን ለማድረግ የሚደረግ የትኛውም ዓይነት ጥረት ሀገር እና ሕዝብን በአደባባይ መካድ ሲሆን ትልቅ ጸጸትን የሚያስከትልም ነው።

ከዚህ አኳያ በቀጣናው ያሉ ሀገራት መንግሥታት አካባቢውን ከግጭት አዙሪት በመታደግ ፍትሐዊ የጋራ ተጠቃሚነት በማስፈን፤ የሀገራቱን ሕዝቦች የሰላም እና የልማት ጥያቄ ለመመለስ በኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት የተጀመረውን መነሳሳት በአግባቡ ተረድተው ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለጋራ የሕዝቦች ፍትሐዊ ተጠቃሚነት

ግርማ መንግሥቴ

የአፍሪካ ቀንድ ጉዳይ ሁሌም የሁሉም አጀንዳ ነው። አካባቢው ያላነጋገረበት ጊዜ ስለ መኖሩ ማስረጃ እንደ ሌለ ሁሉ፤ ስለ አካባቢው ጉዳይ ችላ ያለ አካል ካለም ራሳቸው፤ የአካባቢው ሀገራት እንጂ ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም።

አካባቢው በማንኛውም ፀጋ ተፈጥሮ አብዝታ ያደለችው ፣ ግን ደግሞ ተፈጥሮ የሰጠቻቸውን ፀጋ በአግባቡ መጠቀም ካልቻሉ የዓለማችን አካባቢዎች በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው። እያላቸው የሌላቸው ከሆኑ ሀገራት ሁሉ ፊት መሪው ይኸው የቀንዱ አካባቢ እንጂ ሌላ ሊሆን አልቻለም።

አላዋቂነቱን ባለማወቅ አዋቂ መስሎ እርስ በእርሱ ላለመተዋወቅ የሚጥር ትንግርተኛ አካባቢ ካለ እሱ የቀንዱ አካባቢ እንጂ ሌላ ሆኖ አያውቅም። "ተፈጥሯዊ መነሻና ምክንያት ያለውን 'ሰጥቶ መቀበል' መርህ መቀበልም ሆነ መለማመድን የተጠየፈ ከባቢ ይኖር ይሆን?"

ለጥያቄው መልሱ ያለ ምንም ማወላወል "አዎ" ይሆንና፤ ማብራሪያውም፣ ዝቅ ብለን የምንመለከተው እንዳለ ሆኖ፣ "የአፍሪካ ቀንድ" የሚል ከመሆን አያመልጥም። ይህንን የሚጠራጠር ካለ እሱ አካባቢውን የማያውቅ ነውና ልናልፈው ግድ ይሆናል።ይህ ሁሉ ውርጅብኝ መሰል ሀቲት "ለምን?" የሚል ጥያቄን ካስነሳ ምክንያቱን እንደሚከተለው እናመላከታለን።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ጂቡቲ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን እና ሶማሊያን ያካተተው፤ በበርካታ የጂኦ-ፖለቲካ ፍጥጫዎች የተሞላው ከፊል የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን የሚያካትተው የአፍሪካ ቀንድ በየጊዜው የሰላ አስተያየት ከሚሰጥባቸው ቀጣናዎች መካከል ቀዳሚው ነው።

አብዛኞቹ አስተያየቶች ደግሞ አሉታዊ እንጂ አዎንታዊ ገፅታም ሆነ አንድምታ የላቸውም። ሁሉም በሚባል ደረጃ አካባቢው በተለያዩ (በአብዛኛው) ሰው ሰራሽ ችግሮች ሲታመስ የኖረና እየኖረም ያለ አፍሪካዊ ክፍል ነው።

በዚሁ ዓመት (ጥር 2024) "ፈንድ ፎር ፒስ" የተባለው ተቋም እንደገለጸው፤ በዓለማችን መረጋጋታቸው በቀላሉ ሊናጋባቸው ከሚችሉ ቀጣናዎች መካከል አንዱ ሲሆን፤ የአፍሪካ ቀንድ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የሚያልቁባቸውን ጦርነቶች የሚያስተናግድ ቀጣና ነው።

በዜጎች መብት ጥሰት ስማቸው በክፉ የሚነሱ ሀገራት መሪዎች መገኛ ከሆኑ አካባቢዎች መካከልም አንዱ የአፍሪካ ቀንድ ነው። አካባቢው ውጥረት የማያጣውና በሀገራት ውስጣዊ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በሀገራቱ በራሳቸው መካከል የእርስ በእርስ ግንኙነት መሻከርም የሚታወቅ ነው።

በሚሊዮኖች የሚፈናቀሉበት ፣ በመቶ ሺዎች ህይወታቸው የሚቀጠፍበት ፣ በቢሊዮን ዶላር የሚገመት ንብረት የሚወድምበት ቀጣና ነው። ያሳዝናል።አካባቢው ተፈጥሮ ባደለችው ፀጋ ምክንያት ሌሎች አንድ ሆነው ሊቀራመቱት ሲመጡ እሱ ለራሱ አንድ መሆን ያቃተው አካባቢ ነው።

እራሱን ለተቀራማቾች እያመቻቸ ዓመታትን በቀውስና ግጭት ውስጥ እንደ ሰጠመ የሚገኝ ነው፤ አንድ ሆኖ እርስ በርሱ በመረዳዳት ሊያገኝ የሚችለውን የጋራ ጥቅም ለሌሎች "እነሆ በረከት" ማለትን የመረጠ ታሪከኛ አካባቢ ነው።

ሰሞኑን (ጥቅምት 30) ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ አድርገው የነበሩት ደራሲና የታሪክ ተመራማሪው አቶ ዳኛው ገብሩ ተስፋው እንደነገሩንም ሆነ እኛም እንደምናስተውለው የቀንዱ ሀገራት አንድ የመሆን፤ አንድም ሆኖ በጋራ የመሥራትና የመጠቀም ችግር ይስተዋልባቸዋል።

ይህ ደግሞ ከምንጊዜውም በላይ አሁን እየታየ ያለ እውነት ነው።ቀይ ባህርን ዋቢ አድርገው የአካባቢውን ሀገራት የሚወቅሱት አቶ ዳኛው እንደሚሉት፤ ቀይ ባሕር፤ 24 ሰዓት የማያንቀላፋ፣ 24 ሰዓት የሚያንቀላፉና ችግር ጠማቂዎች ያሉበት ቀጣና ነው። እንዲህ ሲባል አንደኛ 24 ሰዓት አፍጥጠው የሚከታተሉ ሀገሮች አሉ።

እንደሚስተዋለውም ሁሉም በሚያስብል ደረጃ ተረባርቦ በቀይ ባሕር አካባቢ ከጂቡቲ እስከ ሶማሊያ ድረስ ወደብና የጦር ሰፈር እየተከራየ የተቀመጠበት ሁኔታ አለ። [***] አፍሪካንና የኢስያን ኢኮኖሚ ሊቀራመቱ፣ ሰፊ የሆነውን የሰው ጉልበት ሊበዘብዙና ገበያውን ሊጠቀሙ የሚችሉ ሀገሮች 24 ሰዓት አይናቸውን ከቀይ ባሕር ላይ አይነቅሉም፤ አያሸልቡምም።

ሁለተኛው ደግሞ 24 ሰዓት የሚተኙት ናቸው፣ እነዚህም የአካባቢው ሀገሮች ናቸው ማለት ይቻላል። ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ የመንም እንቅልፋሞች ናቸው። እነዚህ የአካባቢው ሀገራት እንቅልፋም ባይሆኑ ኖሮ፤ በተናጠል ጥቅማቸውን ማስከበር ባይችሉም፤ ሕብረት በመፍጠር ጥቅማቸውን ያስከብሩ ነበር።

አቶ ዳኛው የቀንዱን ሀገራት በሌላም ጉዳይ ይወቅሷቸዋል። የ"ሰጥቶ መቀበል" መርህን ያለመቀበላቸውን በማንሳት፤ ይህንንም ሀገራችን ሰጥቶ በመቀበል መርህና ፍትሐዊ በመሆን ጥቅም የምታምን ናት። ጎረቤቶቻችንም ሰጥቶ መቀበልን መለማመድ አለባቸው።

ጎረቤቶቻችን ከእኛ የሚያገኙት ብዙ ነገር አለ። በዚያው ልክ ልናሳጣቸውም የሚያስችለን በርካታ ነገር አለ። ለምሳሌ ሶማሊያን ብንወስድ ሕልውናዋ የተመሰረተው በኢትዮጵያ ወንዞች በዋቤ ሸበሌና በገናሌ ላይ ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ ገና በእነዚህ ወንዞች ላይ ያልተጠቀመች ናት።

የሶማሊያ ሕልውና በኢትዮጵያ ወንዞች ላይ የተንጠለጠለ ሆኖ ሳለ፤ ሶማሊያዎች እኛን ባሕር ሊከለክሉን አይገባም። ሰጥቶ መቀበል ካቃታቸው እኛም ያለመስጠት መብታችን የተጠበቀ ነው ይላሉ። አንድ ሆኖ በሰጥቶ መቀበል መርህ መሰረት የጋራ ተጠቃሚ መሆን እየተቻለ፤ የቀንዱና የሌሎች የአፍሪካ ሀገራትን ከዚህ ውጪ ሆኖ ማፈንገጥን በተመለከተም ራስ ገዟ ሶማሌላንድ ለኢትዮጵያ የባሕር በር ሰጠች ተብሎ የዚያን ያህል ማለቃቀስ አያስፈልግም ባይ ናቸው።

ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር ስለተዋዋለች የተለያዩ ጠላቶችን በዙሪያቸው እየጠሩ የሚያሰባስቡና ኅብረት የሚፈጥሩበት አካሄድ እራሳቸውን አንቀው እንደመግደል የሚቆጠር መሆኑን ሊረዱ እንደሚገባም አመልክተዋል። የዚህ ጽሑፍ አቢይ ጉዳይም ይኸው ነው ።

የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት በጋራ ጉዳይ ላይ አንድ ሆነው ሊቀራመቷቸው የሚቋምጡትን ሁሉ በማሳፈር የጋራ ተጠቃሚ መሆን ሲችሉ፤ ጭራሽ በአካባቢው ጎላ ብላ የምትታየውን ኢትዮጵያ ከሰጥቶ መቀበል መርህ እንድታፈነግጥ የማድረግ እንቅስቃሴ ላይ ተጠምደው የመታየታቸው ጉዳይ የማይጠቅማቸው መሆኑን ማሳየት ነው።

ዘፋኞቹ "ሁሉም ቢተባበር / የት ይደረስ ነበር" እንዳሉት፤ የቀንዱ ሀገራት ከተዘፈቁበት የእርስ በርስ ሽኩቻ በመውጣት አንድ ሆነው በአንድነት ለጋራ ተጠቃሚነት ቢሰሩ የት በደረሱ ነበር፤ በርግጥ አሁንም አልመሸም እውነታውን በቅን ልቦና ተረድተው፤ ለጋራ ፍትሀዊ ተጠቃሚነት አብረው በመስራት የድህነት እና የኋላ ቀርነት ታሪካቸውን መለወጥ፤ የሕዝቦቻቸውን ብሩህ ነገዎችን መፍጠር ይችላሉ !?

ዜና

# በአማራ ክልል በገጠር ክላስተር የተደራጁ ተቋማት እያከናወኑ ባሉት የልማት ተግባራት ለውጥ እያመጡ ናቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በገጠር ክላስተር የተደራጁ ተቋማት የሕዝቡን ጥያቄ ለመመለስ እያከናወኑ ባሉት የልማት ተግባራት ለውጥ እያመጡ መሆኑን በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ ድረስ ሳህሉ (ዶ/ር) ገለጹ።

የገጠር ክላስተር ተቋማት የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ዕቅድ አፈፃፀም የገመገመና ቀጣይ አቅጣጫ ላይ የመከረ መድረክ ትናንት በባህር ዳር ከተማ ተካሂዷል።

ዶክተር ድረስ ሳህሉ፤ በክልሉ የገጠር ኢኮኖሚ ልማት 80 በመቶ የሚሸፍኑ ተቋማት በክላስተር ተደራጅተው በቅንጅትና በትብብር እየሰሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በዚህም በመንገድና ውሃ ተደራሽነት፣ በማዕድን ሀብት ልማት፣ በግብርና ምርታማነት እድገትና ሌሎች ተያያዥ የልማት ስራዎች ለውጥ እያመጡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ተቋማቱ ስራዎችን በቅንጅት መምራት መጀመራቸው የሕዝቡን የልማት ጥያቄ ውጤታማ በሆነ መንገድ መመለስ እንደሚያስችል አመልክተዋል።

ቅንጅታዊ አሰራሩ በዕውቀት ሽግግር፣ የሰው ኃይልንና ሌሎች ሀብቶችን በቁጠባ በመጠቀም ብሎም የስራ ድግግሞሽን በማስወገድ አበረታች ለውጥ ማስመዝገብ መቻሉን አስታውቀዋል።

ይህም በዘንድሮው የበጋ ወቅት በክልሉ ያለውን የውሃ ሀብት አቅም በመጠቀም ከ340 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ማልማት የሚያስችል መሰረት መጣሉን አስረድተዋል።

ከዚህ ውስጥ 254 ሺህ ሄክታሩ በበጋ ስንዴ እንደሚለማ ጠቁመው፤ እስካሁንም በአጠቃላይ ከሰባት ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር መሸፈኑን ገልጸዋል።

የክልሉ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ኃላፊ ዳኘነት ፈንታ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በበጀት ዓመቱ 23 ሺህ ሄክታር መሬት ማልማት የሚያስችሉ 156 የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ እየተከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም 82 ሺህ ሄክታር መሬት ማልማት የሚያስችሉ የ110 የመስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ስራም እንዲሁ።

በበጀት ዓመቱ ወረዳን ከወረዳና ከቀበሌዎች የሚያገናኙ 38 አዲስ የመንገድ ፕሮጀክቶች ግንባታ ስራ ለማከናወን ታቅዶ ወደ ስራ ለመግባት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የገለጹት የክልሉ ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ቀለሙ ሙሉነህ ናቸው።

ሰላምን ከማስከበሩ በተጓዳኝ የመንገድ ልማቱን ተደራሽ ለማድረግ ከክላስተሩ ተቋማት ጋር በመተባበር እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል።

በመድረኩ የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አብዱ ሁሴን(ዶ/ር) እና የክላስተር ተቋማት አመራር አባላትና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

# ኢትዮጵያ 20ኛውን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጉባኤው በየሁለት ዓመቱ በተለያዩ ሀገራት የሚካሄድ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ የዘንድሮውን ጉባኤ አዘጋጇ ኢትዮጵያም ዝግጅት እያደረገች መሆኗን አስታውቀዋል።ጉባዔው የኮንስትራክሽን፣ የመሠረተ ልማትና ሌሎች ኢንቨስተሮች የሚሳተፉበት በመሆኑ ሰፊ የሥራ እድል ለመፍጠር ምቹ አጋጣሚ መሆኑንም ገልጸዋል።

ሀገራት እንደ የመኪና መንገድ፣ የባቡር ሀዲድ፣ አየር መንገድ፣ ግድብ፣ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የከተማና የገጠር መሰረተ ልማት ዝርጋታ ባሉ ትላልቅ መሰረተ ልማቶች ላይ ተሞክሮ የሚቀስሙበትና ለሥራ እድል ፈጠራም በጉባዔው አስቻይ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱበት እንደሚሆንም ነው የጠቀሱት፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ጉባኤው ከተለያዩ የዓለም ሀገራት የተወጣጡ የፖሊሲ አማካሪዎች፣ የፖሊሲ አውጪዎች፣ የንግድ ዘርፍ ማህበራት ተወካዮችና ባለ ድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ነው።ሰፊ የሥራ እድል ሊፈጥሩ በሚችሉ የመሰረተ ልማት ክንውኖች ላይ ሰፊ ውይይቶች ይደረጋሉ።ይህም ለሥራ እድል ፈጠራ ትልቅ ሚና ያለው ነው።ጉባኤው የተሳካ እንዲሆንም 15 የመንግሥት ተቋማት ኮሚቴ በማቋቋም ወደ ሥራ መግባታቸውን ተናግረዋል፡፡

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከመሆኗ ባሻገር የአፍሪካዊያን መቀመጫ እና የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ ማዕከል በመሆን የተለያዩ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ጉባዔዎችን እያስተናገደች መሆኗን ጠቅሰዋል።ዓለም አቀፍ ጉባዔዎችን የማስተናገድ ሚናዋ ተጠናክሮ ይቀጥላልም ብለዋል።

የዓለም የሥራ ድርጅት የምሥራቅ አፍሪካ ዳይሬክተር ኩምቡላ ንዳባ በበኩላቸው፤ ጉባዔው ለኢትዮጵያ በርካታ እድሎችን እንደሚሰጥ ገልጸዋል። የመሠረተ ልማት ዝርጋታን ጨምሮ የኢትዮጵያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ስኬት ተሞክሮ ለሌሎች የማሳየት ፋይዳ እንዳለው ጠቅሰዋል።ኢትዮጵያ በወጣቶች የልማት ፕሮግራሞች አጠቃቀም ላይ ያላትን የረዥም ጊዜ ልምድ እንደምታካፍልም ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ባህላዊ ቅርሶችን ፣ተፈጥሮአዊ ውበቶችን እና ጉልህ ታሪካዊ አሻራዎችን ያቀፈች ሀገር በመሆኗ ከጉባዔው ጎን ለጎንም እነዚህን የቱሪስት መዳረሻዎች የመጎብኘት እድሎች እንዳሉ ጠቅሰዋል፡፡

ጉባዔውን በዋናነት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም የሥራ ድርጅት ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በትብብር የሚያዘጋጁት ሲሆን፤ በኢትዮጵያ በኩል የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሚያስተባብሩት መሆኑ ታውቋል።

# የነፃ አገልግሎቱ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በዓለም ላይ ከሚከሰቱ እርግዝናዎች 61 በመቶው በውርጃ ይጠናቀቃሉ ያሉት ባለሙያዋ፤ የእንዲህ ያሉ ጥናቶች ትኩረት ካደጉት ሀገራት ይልቅ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ላይ መሆኑን ያስረዳሉ። በኢትዮጵያም ከህክምና ተደራሽነት ችግር፣ ከግንዛቤ እጥረት፣ ከሴቶች አለመማር፣ ከያለዕድሜ ጋብቻና ከሌሎችም ችግሮች አንፃር ያልተፈለገ እርግዝናና ውርጃ መጠን ከፍ ያለ ሊሆን እንደሚችል ያነሳሉ።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ ከእርግዝና በፊት ጀምሮ እስከ ከወሊድ በኋላ እስካለው አንድ ሺህ ቀናት ድረስ ያለው አገልግሎት ላይ የሚሰራ ራሱን የቻለ ዘርፍ እንዳለውም ይገልፃሉ። ስለሆነም የአገልግሎት ተደራሽነቱን ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከዛ ባሻገር ለህብረተሰቡ ግንዛቤ መስጠት ላይ በተለይ ሚዲያው መስራት እንዳለበት ገልጸው፤ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የተለያዩ የንቅናቄ መድረኮችን እስከ ቀበሌ ድረስ በማዘጋጀት የጎሳ መሪዎችን፣ የሃይማኖት አባቶችን እንዲሁም ለህብረተሰቡ ወሳኝ የሚባሉ አካላትን በማሳተፍ ውይይት እያደረጉ እንደሚገኙ ያስረዳሉ። የሕዝብ ተወካዮች አባላትም በተመረጡባቸው አካባቢዎች የቤተሰብ እቅድ ሀገራዊ ጉዳይ በመሆኑ ድጋፍ በማድረግና በጀት በማስመደብ እንዲሰሩ ለማድረግ የተለያዩ መድረኮች እየፈጠሩ እንደሚገኙ ያብራራሉ።

የጤና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ኃላፊ የሆኑት ዶክተር ተገኔ ረጋሳ በበኩላቸው፤ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫዎች አንዱ መሆኑን ገልጸው፤ በጉዳዩ ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር የአገልግሎት ተደራሽነቱን ለመጨመር ከመገናኛ ባለሙያዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደእርሳቸው ገለፃ በተለይ የሚዲያ ባለሙያዎች ግንዛቤ በመፍጠርና የአገልግሎት ተደራሽነቱን በመጨመር ረገድ ያላቸው ሚና ከፍ ያለ በመሆኑ በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በስነተዋልዶና በሌሎች የጤና ጉዳዮች ዙሪያ በየጊዜው የተለያዩ ስልጠናዎችን እየሰጠ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

# የአምራች ኢንዱስትሪው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ምርታማነትን ማሳደግ አዳጋች ይሆናል።

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ የተሰማሩ አምራቾች እየገጠማቸው ያለው ማነቆ ምንድን ነው? ያሉትን ችግሮችስ መፍቻ መንገዶች ምንድን ናቸው? ሲል ኢፕድ ጠይቋል።

በአማራ ክልል የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሱሌማን ኢብራሂም እንደሚሉት፤ የማኑፋክቸሪንግ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ መሟላት ያለባቸው ነገሮች አሉ። ካልተሟሉ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚባለው ነገር የማይታሰብ ነው።

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተሰማርቶ ለማምረት የፋይናንስና የማምረቻ ቦታ እጥረት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦት፤ የመሰረተ ልማት ችግር እንዲሁም የሀገር ውስጥ ምርትን እራሱ መንግሥት ያለመጠቀም ማነቆዎች አሉ ይላሉ።

አምራቾች ገንዘብ እያላቸው ወደ አገልግሎት ዘርፍ የሚገቡበት በርካታ ምክንያት አላቸው የሚሉት አቶ ሱሌማን፤ አምራች ዘርፉ በአጀማመር ወቅት በርካታ ወጪዎች እንዲሁም ጊዜ እንደሚጠይቅ ያስረዳሉ።

በዚህም ምክንያት የዘርፉ ተዋናዮች ወይም ዘርፉን መቀላቀል የሚፈልጉ አካላት ወደ ማምረት ከመግባት ይልቅ ወደ አገልግሎት መግባት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ ይላሉ።

አምራቾች እንደምንም ተፍጨርጭረው ማሽን አምጥተው ስራ ይጀምራሉ፤ ባለው የሰለጠነ የሰው ኃይል፤ በሀይል አቅርቦት፤ በመሰረተ ልማት ችግሮች እየተዳከሙ ይሄዳሉ፤ ምርትና ምርታማነትም እየቀነሰ ይሄዳል ሲሉ ይገልጻሉ።

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ፈትቶ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በአካባቢው ያለው አስተዳደር ያለውን የማምረቻ ቦታ እጥረት መፍታት፤ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ችግርን መቅረፍ፤ ባንኮች ያለውን የፋይናንስ ችግር ማስወገድ፤ ዘላቂ መፍትሔ የሚሰጥ አሰራር መዘርጋት ተገቢ መሆኑን አፅንዖት ይሰጣሉ። ከቴክኒክና ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል በመቅጠር የሰው ኃይል እጥረትን መፍታት እንደሚገባም ይጠቁማሉ።

ማኑፋክቸሪንጉን አበረታትቶ በሚፈለገው ልክ ለማሳደግ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ከውጪ የሚያስመጡትን ምርት ትተው በሀገር ውስጥ የሚመረትን ምርት መግዛት እንዳለባቸውም ነው የሚያስገነዝቡት።

እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ክልል የሀገርን ምርት መጠቀም መመሪያ ሆኖ ሊወርድ እንደሚገባ በመጠቆም፤ በኢትዮጵያ ታምርትና የኢትዮጵያን ይግዙ ንቅናቄ የመንግሥት ተቋማት የሀገር ውስጥ ምርትን ገዝተው በማሳየት ለዜጎች ግንዛቤ መፍጠር እንደሚኖርባቸው ነው የተናገሩት።

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ የፋይናንስና የማምረቻ ቦታ እጥረት፤ የመሰረተ ልማት፤ የሰለጠነ የሰው ኃይል፤ የኃይል አቅርቦት ችግሮች ይስተዋሉበታል የሚሉት ደግሞ የኦሮሚያ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ አበበ በንቲ ናቸው።

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተስተዋሉ ያሉ ማነቆዎችን መፍታት አስፈላጊ ነው ይላሉ አቶ አበበ።

መንግሥት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እየሰራ ያለው ስራ ጥሩ መሆኑን የሚያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ መንግሥት ተግባራዊ እያደረጋቸው የተለያዩ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች እስከ ታች ወርደው ተግባራዊ መደረግ ይኖርባቸዋል ሲሉ ይጠቅሳሉ።

ሠራተኛን አሰልጥኖ ወደ ኢንዱስትሪው የማምጣት፣ ከባንኮች፣ ከተለያዩ ልማት ድርጅቶችና ከመንግሥት መዋቅር ተሳስሮ የመሥራት ጉዳይ ላይ ክፍተት መኖሩን የሚያነሱት አቶ አበበ፤ ማኑፋክቸሪንጉን ለማሳደግ፣ ማነቆዎችንም ለመፍታት በቅንጅት መስራት ተገቢ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

የሠራተኛውን ደህንነት መጠበቅ፣ የመሰረተ ልማት ችግሮችን፣ የፋይናንስ እጥረትን መፍታት ከተቻለ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ላይ እየተሰራ ያለው ስራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትልቅ ውጤት የሚያመጣ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዳይሬክተር አቶ አብዱልፈታ የሱፍ በበኩላቸው፤ ኢንዱስትሪው ውስብስብ ችግር ያሉበት ዘርፍ መሆኑን ያነሳሉ።

በዘርፉ የሚታየውን የፋይናንስ ችግር ለመፍታት ለማኑፋክቸሪንግ የሚሰጠው ብድር እንዲጨምር የማድረግ፤ ልማት ባንክንና የተለያዩ የብድር ዘዴዎችን በመክፈት 80 በመቶ ብድር የማቅረብና ብድራቸውን ከፍለው ሲጨርሱ ቦታውን እንዲወስዱ የማድረግ ስራ እየተሰራ መሆኑንም ያብራራሉ።

በኢንዱስትሪው ዘርፍ ላይ ያለውን የማምረቻ ቦታ እጥረት ለመፍታት የማኑፋክቸሪንግ ክላስተሮችን የማስፋት ስራ የመስራት፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሀገር ውስጥ አምራቾች ገብተው እንዲሳተፉ የማድረግ ስራዎችም እየተከናወኑ መሆኑን ያስረዳሉ።

ክልሎች የራሳቸውን ክላስተር በመገንባት ኢንዱስትሪዎች በክላስተር ገብተው እንዲሰሩ የማድረግ ስራ እየተሰራ እንደሚገኝ በመጠቆም፤ በዚህም አሰራር በርካታ ኢንዱስትሪዎች ለምተዋል፤ ምርትም እያመረቱ ይገኛሉ ይላሉ።

በተጨማሪም የማምረቻ ቦታ እጥረትን ለመፍታት ባለሀብቶች ሼዶችን እየሰሩ ለአምራቾች እንዲያከራዩ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ላይ ያሉ ማነቆዎችን ለመፍታት ሰፊ ስራ እየተሰራ ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

መንግሥት የሀገር ውስጥ ምርትን የመጠቀም ባህል እንዲዳብር ምርቶችን ገዝቶ ከመጠቀም ባሻገር ለሀገር ውስጥ አምራቾች ልዩ የግዥ ሥርዓት የመፍጠር፣ እንዲሸጡ የማድረግ፣ የመንግሥት ተቋማትም ገዝተው እንዲጠቀሙ የማበረታታት ስራ እየሰራ ይገኛል ሲሉ ይናገራሉ።

የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ላይ የሚታዩ ማነቆዎችን በመፍታት ጥራት ያለው ምርት በማምረት ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ እየተሰራ ያለው ስራም ውጤት እያስገኘ ነው ሲሉ ነው ያብራሩት።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# መጽሐፍ አዟሪው፡ገጣሚ

**ሰሚራ በርሀ**

ወጣትነት ሰፊ ጊዜ ፣ በብዙዎች ዘንድ ተፈላጊነት፣ ብርቱ ጉልበት ብዙ ነገር መፍጠር የሚችል የነቃ አዕምሮ ያለበት ጊዜ ነው፡፡ ስኬትንም ሆነ ውጤታማነትን በዚህ አጓጊ የእድሜ ወቅት ላይ ለማግኘት እነዚህን በረከቶች መረዳት ያስፈልጋል ፡፡ አብዝቶ መሞከር ፣ እድልን መጠቀም ፣ እንደ ብርቱ ጉልበት ሁሉ ተስፋ ለመቁረጥ በፍጹም ያልተዘጋጀ ደንዳና ልብ ይፈልጋል፡፡ የዚህ ጽሑፍ መነሻ ከሁለት « በከንፈርሽ በራፍ » የተሰኘ የራሱን ሶስተኛ የግጥም መጽሐፍ ለሕትመት ያበቃው ገጣሚ እና ፀሐፊ ዮሐንስ ሞላ በፌስቡክ የማህበራዊ ገጹ ያጋራው ጽሑፍ ነው ፡፡

ጽሑፉ አንድ በእጆቹ በርከት ያሉ መጻሕፍትን የያዘ ወጣት ፎቶ አያይዟል፡፡ የራሱን መጽሐፍ ግዙኝ እያለ እሱ በሚገኝበት የመዝናኛ ስፍራ አግኝቶት በማህበራዊ ገጹ ያሉ ሰዎች ጭምር እንዲገዙት የሚያትት እና የሚያበረታታ ነው፡፡ ወጣት ተመስገን ታደሰ ይባላል፡፡ በዛሬው የወጣቶች ገጻችን የራሱን መጽሐፍ እያዞረ እስከ መሸጥ ያደረሰውን አጋጣሚ እና የሕይወት ጉዞ እንዲህ አጋርቶናል፡፡

ትውልድና እድገቱ ምዕራብ ጎጃም ደጋ ዳሞት ወረዳ ውስጥ ጣዕመ በተባለ ትንሽ የቀበሌ መንደር ውስጥ ነው። ለወላጆቹ የመጨረሻ እና አስረኛ ልጅም ጭምር ነው። ሥነ-ጽሑፍ እና ተመስገን ትውውቃቸው ከልጅነት ጀምሮ ነው። ጥሩ የማንበብ ልማድ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ክበቦች ላይ የነቃ ተሳትፎ ነበረው። ትምህርት ቤት የቀለም ትምህርትን መማሪያ ብቻም ሳይሆን ተማሪዎች ያላቸውን ዝንባሌ አውጥተው የሚሞክሩበት በአቅማቸው ራሳቸውን የሚፈልጉበት ሥፍራ ነው፡፡

ታዲያ ተመስገንም የልጅነት ጊዜው ለሚወደው ሥነ-ጽሑፍ እና ግጥም ቦታ የሰጠ ነበርና በተለያዩ ክበቦች ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ በሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ላይ የራሱን የግጥም ሥራዎች ያቀርባል፡፡ የተመስገን ወላጆች ልክ እንደ አብዛኛው ቤተሰብ ኪነ-ጥበብም ሆነ ሥነ-ጽሑፍ ልጆቻቸው እንዲገፉበት የሚፈልጉት ዘርፍ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በዚሁ ከቀጠለ እንዴት ራሱን ማስተዳደር ይችላል የሚል ስጋት ነበራቸው፡፡


ተማሪ ሳለ ህልሙ መሃንዲስ መሆን ነበር። ገጣሚ መሆንንም የሚተወው ጉዳይ አይደለም። ከልጅነቱ ጀምሮ ከሚያነባቸው ገጣሚያን እና ጸሐፍት መካከልም ገጣሚ እና ባለቅኔ ሙሉጌታ ተስፋዬ ወዳጅ ነው፡፡ ታዲያ በትምህርት ቤትም ሆነ በሚኖርበት ከተማ ውስጥ የሚዘጋጁ የተለያዩ የኪነ-ጥበብ መድረኮችን እየተሳተፈ የመሰናዶ ትምህርቱን አጠናቆ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ለመግባት ጊዜው ደረሰ፡፡ የተመደበው እሱ ከሚኖርበት ስፍራ ርቆ የሚገኝ እና ፍጹም የተለያየ አየር ጸባይ ያለው አካባቢ ነበር፡፡

«የተመደብኩበት አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ነበር፡፡ እኔ ያደግሁበት ቦታ ደጋ እና በጣም ቀዝቃዛ ነው። አሶሳ ደግሞ በጣም ሙቀት ነው፡፡» የሚለው ተመስገን በዚያ የነበረው ቆይታ ለመልመድ አንድ ዓመት ያህል ፈጅቶበት እንደነበር ይናገራል፡፡ በዩኒቨርሲቲው ለመማር የመረጠው የትምህርት ዘርፍ የልጅነት ህልሙን ከግምት ያስገባ ነበር፡፡ የሲቪል ምህንድስና ትምህርትን ምርጫው አድርጎ ትምህርቱን መማር ቀጠለ፡፡ ለሥነ-ጽሑፍ ያለውን ዝንባሌም አልተወውም፡፡ «ተማሪ እያለሁ እንደምንቀሳቀሰው ባይሆንም በተለያዩ ክበቦች ላይ እና ጊቢ ውስጥ የሚዘጋጁ መድረኮች ላይ የግጥም ሥራዎቼን አቀርብ ነበር፡፡»

ተመስገን ሃሳቡን የሚገልጽበትን ግጥም በተለያዩ ደብተሮች ላይ በማስፈር እና በማከማቸት ለሌሎች ሰዎች የሚጋራበትን መንገድም ይፈልግ ነበር፡፡ «የምጽፋቸውን ግጥሞች አስቀምጥ ነበር እና በአንድ ወቅት ስመለከተው በጣም ብዙ ሆኖ አገኘሁት፤ ባሳትመው የሚል ሃሳብ መጣልኝ፡፡ ከዚያም ከግጥሞቼ ውስጥ መምረጥ እና ረቂቅ ማዘጋጀት ጀመርኩ፡፡» ይላል፡፡

በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያለው የባሕል እና ቱሪዝም ክፍል በተለያየ ወቅት ዝንባሌ ላላቸው ሰዓሊያን የፊልም ባለሙያዎችን የማገዝ ልምድ እንዳለው ተመስገን መረጃውን አገኘ፡፡ በመሆኑም የግጥም ሥራውን የሚያሳትምበትን አንዱን መንገድ ሞከረ፡፡ የዩኒቨርሲቲው የባሕልና ቱሪዝም ክፍል የመጀመሪያ መጽሐፉን ለሕትመት ለማብቃት እንዲያግዙት ጥያቄውን አቀረበ፡፡ ጥያቄው ተቀባይነት አገኘ፡፡ ያቀረበው የግጥም ጽሑፍ ረቂቅም አልፎ ለሕትመት እንዲበቃ ፍቃድ ቢያገኝም አንድ ጉዳይ ግን ተመስገንን አልተስማማውም፡፡

«መጽሐፉን እንዳሳትም ቢፈቅዱልኝም ግን መጽሐፉ ታትሞ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ብቻ እንዲሆን ነበር



ወጣት ተመስገን ታደሰ፣

የፈቀዱት፡፡ እኔ ደግሞ እንደዛ እንዲሆን አልፈለኩም ነበር፡፡» ሃሳባቸውን በብዕር በኩል ወረቀት ላይ አስፍረው ድርሰት ቢሆን አልያም ግጥም ከሃሳብ ሃሳብ ፤ ከእይታ የተለየ አተያይ እና ቃላት ተመርጦ ደራሲ ጋር ያለን ጽሑፍ ወደ አንባቢ መሳለፍ ለፀሐፊው ልጅን የመውለድ ያህል እንደሆነ ብዙዎች ይገልጻሉ፡፡

ተመስገንም የመጀመሪያ የሆነውን የግጥም መድብሉን ለማሳተም የጀመረው ሂደት ታትሞ እስከሚያየው ድረስ ልቡን ስቅል አድርጎት ነበር። በመሆኑም የራሱን መንገድ ተጠቅሞ መጽሐፉን ለሕትመት አበቃው፡፡ የመጀመሪያው የሆነው የግጥም መድብል እና የመጀመሪያ ዲግሪውን በ2010 ዓ.ም ይዞ ተመረቀ፡፡

«ለማሳተም በጣም ጓጉቼ ስለነበር ልመረቅ ስል ሱፍ ልገዛበት የነበረውን ገንዘብ አነስተኛ ኮፒ ያለው እትም አድርጌ አስመረቅሁት፡፡ ከመጽሐፌ ጋር አብረን ነው የተመረቅነው፡፡» ሲል ሁኔታውን ያስታውሳል፡፡

የመጀመሪያ የግጥም መድብሉ «የጣዕመ ማህጸን» የተሰኘ ሲሆን የምርቃት ሥነ-ሥርዓቱም በተማረበት ክፍል ውስጥ ከተማሪ ጓደኞቹ እና ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጋር በመሆን ነበር፡፡ ጣዕመ ተመስገን ተወልዶ ያደገባት የመንደር ቀበሌ ስትሆን የተሰየመችውም ከተማውን በጃንሆይ አጼ ኃይለሥላሴ ወቅት ያስተዳድሩ የነበሩ ብዙ ሥራዎችን የሰሩ ነገር ግን ብዙ ያልተወራላቸው ደጃዝማች ጣዕመን ለመዘከር በማሰብ የተሰየመ ርዕስ ነው፡፡ «የታተመው ትንሽ ኮፒ ቢሆንም ግን በጊዜው ደስተኛ ነበርኩ፡፡ ታዋቂ የሆኑ እንደ ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም፣ ገጣሚ ምስራቅ ተረፈ ያሉ የኪነ-ጥበብ ሰዎችን ተዋውቄበታለሁ፡፡» ይላል፡፡

የተመስገን የመጀመሪያ ዲግሪ እና የመጀመሪያ የሆነው የመጽሐፍ ሥራው የጣዕመ ማህጸን አብረው የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ቆይታቸውን ጨርሰው ወጡ፡፡ ተመስገን የቀረውን የመጽሐፍ እትም ይዞ ወደ ተወለደባት ከተማ በመሄድ ቀሪውን በዚያ ለሚገኙ ጓደኞቹ እና የተለያዩ የኪነጥበብ ማህበራት ላይ መጽሐፉን ለማስተዋወቅ ችሏል፡፡

የዩኒቨርሲቲ ቆይታውን ካጠናቀቀ በኋላ ቀጣዩ ምዕራፍ ሥራ መፈለግ ነበር፡፡ ትምህርቱን ያጠናቀቀው በሲቪል ምህንድስና በመሆኑ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር አንድ ለአምስት በመደራጀት ከመንግሥት የሚሰጣቸውን የተለያዩ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በኮንትራት ተቀብለው ሰርቶ አጠናቅቆ የማስረከብ ሥራን ጀመሩ፡፡ በዚህ ሥራ የተመስገን ኃላፊነት ምንም እንኳን የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ቢሆንም ነገር ግን ቆሞ ማዘዝን በፍጹም አይፈልግም፡፡ «እኛ ከሌሎች የግል ኮንትራክተሮች ጋር የመጫረት አቅም ስለሌለን መንግሥት ነው ፕሮጀክቱን እና የተቆረጠ መሥሪያ ገንዘቡ ይሰጠናል። ስለዚህ ሁላችንም እኩል እንሠራለን ፤ ሠራተኛ ቀጥረን የምናሠራው የማንችለውን ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ኢንጂነር ሄልሜት ለብሰን የምናሰራ ከሆነ የምናተርፈው ገንዘብ አይኖረንም፡፡» በማለት የነበራቸውን ሥራ ትጋት ያስታውሳል፡፡

ተመስገን የጀመረው አዲስ ሥራ ፕሮጀክት በመሆኑ አንድ ፕሮጀክት ሰርተው ካጠናቀቁ በኋላ ሌላ ፕሮጀክት እስኪሰጣቸው ድረስ ሰፊ የሆነ ጊዜን ያሳልፉ ነበር። በመሆኑም ይህንን ትርፍ ጊዜ ተመስገን ሌላ ተጨማሪ ትምህርት በርቀት መርሀ ግብር የአካውንቲንግ ትምህርትን በድጋሚ መማር ቀጠለ፡፡

ሕይወትን በተሻለ መንገድ ለመምራት የተለያዩ መንገዶችን የሚሞክረው ተመስገን በዚህ መሀል ተሰጥኦው የሆነውን የግጥም ሥራዎቹን እየጻፈ ማስቀመጡን እንዲሁ አልተወም፡፡ በኮንስትራክሽን ሥራው የሚያገኘውን ገቢ በማስቀመጥ እና በማጠራቀም ሁለተኛ መጽሐፉን ለማሳተም አገዘው። «50 በመቶ ለማሳተም የሚያግዘኝ ሰው አግኝቼ ነበር። ነገር ግን ለማሳተም ሕትመት ቤት ከተስማሙ በኋላ ሃሳባቸውን ቀየሩ፡፡» በማለት ወቅቱን የሚያስታውሰው ተመስገን ሊያሳትም ከነበረው የእትም ብዛት በግማሽ በመቀነስ ሁለተኛ መጽሐፉ የሆነው «አለት ያጣ ንስር » የግጥም መድብል በ2014 ዓ.ም እንዲታተም አደረገ፡፡

«ተወልጄ ባደግሁበት ከተማ የወጣት ማህበር አለን እና ማህበሩ በሚሰበሰብበት ወቅት ሌሎች የሚመጡ እንግዶች ባሉበት ተመርቋል፡፡» ተመስገን እነዚህን ሁለት መጽሐፎች ሲያሳትም ራሱ አሳትሞ የሚገዙ ሰዎችም ካሉ የሚገዙት ከራሱ ከፀሐፊው እጅ ነበር፡፡ «አሳታሚዎች መጽሐፉን ተቀብለው መሸጥ ይፈልጋሉ ግን ቅድመ ክፍያ አይሰጡም፡፡ መጽሐፉ ከተሸጠ በኋላ ነው የሚከፍሉት። የግጥም መድብል ሲሆን ደግሞ ሰዎች አይገዙም የሚል ሃሳብ ስላላቸው ለመግዛት ፍቃደኛ አይደሉም፡፡» ሲል መጽሐፍ ጽፎ ለመሸጥ ያለውን ውጣውረድ ይናገራል፡፡

ተመስገን የሕትመት ዋጋ መጨመር ፣ ከታተመ በኋላ ተቀብለው የሚሸጡ የመጽሐፍት መደብሮችን አለማግኘት ከባድ ፈተና እንደሆነ ተመስገን ይገልጻል።

የሁለተኛ መጽሐፍ እትም እንዳበቃ ተመስገን በርቀት ይማር የነበረውን ትምህርት አጠናቀቀ፡፡ ቀጣዩ ሃሳብም አዲስ አበባ የምትኖር እህቱ ጋር በመምጣት በዚህ የተማረው የአካውንቲንግ ትምህርት ሥራውን መፈለግ ጀመረ፡፡ «መጀመሪያ የተማርኩት ሲቪል ኢንጂነሪንግ ቢሆንም አሁን ላይ የምተዳደርበት ግን ሁለተኛ ላይ በተማርኩት ትምህርት ነው፡፡» ተመስገን በመገረም የሚያነሳው ሃሳብ ነው፡፡

ወደ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ ባገኘው የባንክ ሥራ ሕይወቱን መምራት ጀመረ፡፡ ነገር ግን የግጥም ሥራውን አልተወውም ነበር፡፡ በተለያዩ የማህበራዊ ገጾች ላይ ግጥሞቹን ማንበብ እና የኪነጥበብ መድረኮች ላይ ሥራዎቹን ማቅረብ ጀመረ፡፡ ተመስገን ጽሑፍ ከልጅነቱ ጀምሮ የሚወደው በመሆኑ የሁለተኛ መጽሐፉን ሁለተኛ እትም በድጋሚ ለማሳተም አሰበ። « ለሁለተኛ ጊዜ ለማሳተም የፈለኩበት ምክንያት የመጀመሪያው እትም የሚስተካከሉ እንከኖች ነበሩት። የተሸጠውም እኔ ባደግሁባት ከተማ ብቻ በመሆኑ ከብዙ ሰው ጋር አላስተዋወቀኝም ነበር፡፡»

የግጥም መጽሐፍን በራስ ወጪ ማሳተም እና ለገበያ ማውጣት ያለውን ፈተና ተመስገን አስቀድሞ የተረዳ ቢሆንም ነገር ግን ከመሞከር ወደኋላ ማለት እና ህልሙን መተውን አልፈቀደም፡፡

«ለሁለተኛ እትም የሚሆነኝን ገንዘብ ከመሥሪያ ቤቴ የሶስት ወር ደሞዝ አስቀድሜ በመውሰድ ነበር ያሳተምኩት፡፡» የሚለው ተመስገን መጽሐፉን ካሳተመ በኋላ ራሱ ለተለያዩ የመጽሐፍ መደብሮች ያከፋፍል ነበር፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው በርካታ የሚባል መጽሐፍ በቤቱ ውስጥ ተቀመጠ። ተመስገን በዚህን ጊዜ ነበር ለምን ራሴ እያዞርኩ አልሸጠውም የሚል ሃሳብ የመጣለት፡፡

ታዲያ የራስን መጽሐፍ እያዞሩ መሸጥ አይከብድም ወይ የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም። «የራስን መጽሐፍ አዙሮ መሸጥ ማለት አንድ ገበሬ ዘርቶ የሰበሰበውን እህል ራሱ ወደ ገበያ ወስዶ አልያም እያዞረ ሲሸጠው እንደ ማለት ነው፡፡ የሰው ፊት መቆም ከባድ ሊመስል ይችላል። ግን ፍርሃቱ የሚኖረው ከአንድ እና ሁለት ደቂቃ ያላነሰ ነው፡፡» የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ተመስገን መጽሐፉን እንምግንኛውም የመጽሐፍ አዟሪ መጽሐፉን ለመሸጥ ወሰነ፡፡ በተለያዩ የመዝናኛ ሥፍራዎች በማምራት ኃላፊዎችን የራሱ መጽሐፍ እንደሆነ በመናገርና በማስፈቀድ በቦታው ላሉ ሰዎች ራሱን እያስተዋወቀ መሸጡን ቀጠለ፡፡ አንዳንዴም ከሥራ ቦታው ወደቤቱ በሚሄድበት ጊዜ እግረ መንገዱን በሚያገኛቸው ሆቴሎች ገብቶ ይሸጣል፡፡ «መጽሐፍ አዟሪዎች ሲያገኙን በሥራዬ ገባህ ይሉኛል፡፡ የራሴን መጽሐፍ ግዛኝ ያለኝ ሰውም አጋጥሞኛል፡፡» ይላል፡፡

ተመስገን መጽሐፍን በራሱ የመሸጥ ሥራውን የእረፍት ጊዜውን በመጠቀም የራሱን መጽሐፍ በ10 ወር ጊዜ ውስጥ 800 የሚደርስ መጽሐፍን አዙሮ ሸጧል፡፡ «በጣም ተስፋ አስቆራጭ ነበር፡፡ ምክንያቱም ሰው ቢዚ ነው ገንዘብ ማውጣት አይፈለግም፤ አንዳንዱ ደግሞ ከንፈር የሚመጥም አለ፡፡» ሲል የሁኔታውን አስከፊነት ያስረዳል፡፡

በዚህ ወቅት ልክ እንደሱ ገጣሚ የሆኑ የኪነ ጥበብ ሰዎችን የራሱ መጽሐፍ እንደሆነ ሲነግራቸው በጣም ያዝናሉ፡፡ ተመስገንም የራሱ መተዳደሪያ ሥራ እንዳለው ይነግራቸዋል፡፡ ከእነዚህ ገጣሚያንም ሆኑ ደራሲያን የእርሱን መጽሐፍ ገዝተው ለማበረታታት የራሳቸውን መጽሐፍ በስጦታ እንደሚበረክቱለትም ያስታውሳል፡፡

ተመስገን የመጣበት መንገድ እና ህልሙን ለማሳካት የተጓዘባቸውን መንገዶች እንደ ጥሩ እድል እንጂ እንደ መጥፎ አጋጣሚ አይቆጥራቸውም፡፡ ምክንያቱም በወሰነው ውሳኔ የሚፈልገውን ህልሙን ለማሳካት እና አንድ ርምጃ መራመድ ችሏል፡፡ ለሌሎች ወጣቶችም ህልማቸውን ለማሳካት የሚያግዳቸውንም ከሰዎች የሚሰጣቸውን አስተያየት መፍራት እንደማይገባ ይገልጻል፡፡

ተመስገን አሁን የሚገኝበት የባንክ ሥራ ውስጥ አንድ ዓመት ያህል ጊዜን አስቆጥሯል፡፡ በቀጣይ በዚሁ ሥራ ላይ በመቀጠል በጎን ደግሞ ጥሩ ጥሩ መጽሐፎችን በመጻፍ ሰዎች ፈልገው ገዝተው የሚያነቧቸውን ተወዳጅ የመጽሐፍ ሥራዎች ማሳተም ህልሙ ነው፡፡

# የምድር በረከት

## የማዕድናት አለኝታ ቦታ የሚለየውና ዳታ የሚያመነጨው ኢንስቲትዩት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በኢትዮጵያ የሚገኙ የማዕድን ሀብቶችን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ጥናቶች ይደረጋሉ፡፡ ጥናቶቹም የትኞቹ ማዕድናት የት ቦታ፣ በምን ያህል መጠን እንደሚገኙ የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

የማዕድኑ ምንነትና የሚገኝበት ቦታ ከታወቀ እና ከተለየ በኋላ ለኢንቨስትመንት ክፍት እንዲሆን በዘርፉ መሰማራት ለሚፈልጉ ኢንቨስትሮች /ባለሀብቶች/ ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንድታገኝ ትልቅ ግብዓት በመሆንም ያገለግላሉ፡፡

የማዕድናቱን ምንነትና መገኛ ቦታ ለይቶ ማወቅ ብቻ በቂ ስለማይሆን በጥናቶቹ የተገኙ መረጃዎችን ዘመኑ በሚመጥን መልኩ አደራጅቶ ማስቀመጥም ያስፈልጋል፡፡ በጥናት የተለዩ ማዕድናትን መረጃ በመሰብሰብ አደራጅቶ፣ አጠናክሮና ተንትኖ በዘርፉ ኢንቨስትመንት መሰማራት ለሚፈልጉ አካላት ተገቢ መረጃ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ መረጃ ከማመንጨት በዘለለ መረጃው ዘመኑ በሚፈልገው መንገድ እንዲደራጅና ለመረጃ ፈላጊ አካላት በቀላሉ እንዲደርስ ማድረግ ይገባል፡፡

ማዕድን ለማልማት ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ እና ረጅም ጊዜን የሚጠይቅ እንደመሆኑ በዘርፉ መሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች ወደ ሥራው ከመግባታቸው በፊት ማግኘት የሚገባቸውን ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል።

ይህ ካልሆነ ግን በማዕድን ፍለጋ መስማራት የሚፈልጉ አካላት ለከፍተኛ የሀብት ብክነትና ድካም ሊዳረጉ ይችላሉ፤ ችግሩ በዚህ ብቻ አያበቃም፤ ባለሀብቶች በዘርፉ መሰማራትን እንዳይደፍሩ ያደርጋል፡፡

በሀገሪቱ የማዕድን ሀብቶች ላይ በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች የተደረሰባቸውን ግኙቶች በተመለከተ የተደራጀና የተጠናከረ መረጃ መኖሩ ባለሀብቱ ብዙ ሳይደክም የሚፈልገውን መረጃ በቀላሉ አግኝቶ ወደ ቀጣዩ የልማቱ ተግባር እንዲገባ ያስችላቸዋል፡፡

በማዕድን ዘርፍ ዳታ በማመንጨት ረገድ የረጅም ጊዜ ልምድ ካላቸው ተቋማት መካከል የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት አንዱ ነው። ኢንስቲትዩቱ በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ዋናው ዳታ ማመንጨት ነው፡፡ በዚህም ከ50 ዓመታት በላይ ልምድ ያካበተ ነው፡፡ የማዕድናት የአለኝታ ቦታ ልየታ ጥናት እያደረገ የሚያመነጨውን መረጃ /ዳታ/ በዳታ ማዕከልና በቤተመጻሕፍት /ላይብረሪ/ በማከማቸት መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት በማሰራጨት ተደራሽ እያደረገ ይገኛል፡፡

የዳታ ማዕከሉና ቤተመጻሕፍቱን /ላይብረሪውን/ በዘመናዊ መልኩ በማደራጀት ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን የተሠሩና እየተሠሩ ያሉ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ አደራጅቶና ተንትኖ ለተጠቃሚ በሚፈለገው ልክና መልክ ያቀርባል፡፡ መረጃውን በሶፍትና በሀርድ ኮፒ በማድረግ በቀላሉ ተደራሽ እያደረገም ይገኛል፡፡

ኢንስቲትዩቱ በማዕድን ዘርፉ ላይ ባከናወናቸው በርካታ ተግባሮች አማካኝነት በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ መረጃዎችን ማፍራት ችሏል፤ መረጃዎቹንም ለሚፈልጉ አካላት ተደራሽ አድርጓል፡፡ እነዚህ መረጃዎችም በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች፣ በዘርፉ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ አካላት፣ ከዩኒቨርሲቲዎቹ ወደ ተቋሙ ለሚሄዱ የጂኦሎጂ ተማሪዎች፣ የኢትዮጵያን ጂኦሎጂ ለሚያጠኑ የውጭ ሀገር ተመራማሪዎች እና ሌሎች መረጃ ፈላጊዎች ይሰጣል፡፡ ኢንስትቲዩቱ መረጃውን ለመረጃ ተጠቃሚዎች የሚያደርስበት የራሱ አሠራር ያለው ሲሆን፤ መረጃዎች በነፃ የሚሰጥበትና የሚሸጥበት አሠራር እንዳለው ይታወቃል፡፡



አቶ ኢጃራ ተስፋዬ፣

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ኢጃራ ተስፋዬ ኢንስቲትዩቱ ዋነኛ ሥራ ዳታ ማመንጨት መሆኑን ይናገራሉ። ኢንስቲትዩቱ የረጅም ጊዜ ልምድ ያለው እንደመሆኑ እስካሁን ብዙ ዳታዎችን ማመንጨት እንደቻለ ይገልጻሉ፡፡ ዘንድሮ ብቻ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ዳታዎች ለፈላጊ ባለድርሻ አካላት በመሸጥ ተደራሽነቱን እያሰፋ መምጣቱን አመላክተዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ኢንስቲትዩቱ የማዕድናት አለኝታ ቦታ በመለየትና ዳታ በማመንጨት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው፡፡ የሥነ ምድር መረጃ ሲባል የማዕድን ፍለጋ፣ የጂኦተርማል፣ የሥነ ምድር አደጋ እና የመሳሰሉት ሥራዎች ላይ የተለያዩ ማጥኛ ዘዴዎች ተጠቅሞ ያጠናል። በጥናቱ የተገኘውን መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ያደርጋል፡፡ በዚህ መሠረት የማዕድን አለኝታ ልየታ ጥናት በሚያካሄድበት ወቅት ጥናቱ በሚካሄድባቸው ክልሎች ካሉ ባለሙያዎች ጋር ይሰራል፡፡

የክልል ባለሙያዎች እንዲሳተፉ የሚደረግበት ዋንኛ ምክንያት በመጀመሪያው በማዕድኑ አለኝታ ቦታ ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች የሥራ ላይ ልምድ እንዲወሰዱ ነው፡፡ ሁለተኛው ሥራው ጥያቄ ሊፈጥር የሚችል መሆን ስለሌለበት አብረው ሠርተው እንዲያዩና እንዲያውቁት ለማድረግ ሲሆን፤ ሦስተኛው የማዕድን ልየታ ሥራ ሪፖርት ከተጠናቀቀ በኋላ በአካባቢው ላይ የተደረገው የአለኝታ ቦታ የልየታ ግኝት ውጤት እንዲደርሳቸው የሚደረግበት አሠራርን ተከትሎ እየሰራ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

‹‹ኢንስቲትዩት በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት እስካሁን ባመነጨው የሥነ ምድር ዳታ መጠን ልክ ያመነጨ ሌላ ተቋም የለም። ጥናቶችን በጥልቀት በመሥራትም ይታወቃል። የእያንዳንዱ ማዕድን ክምችት መረጃው በአግባቡ ተሰብስቦ፣ ተደራጅቶና ተተንትኖ በላይብረሪ እንዲቀመጥ ተደርጓል። በወርቅ፣ በክሮማይት፣ በኒኬል፣ ሊትየም፣ ጂኦተርማል እና በሌሎችም ረገድ የተደረጉ ጥናቶችና የተገኙ ላቦራቶሪ ግኝቶችን የተመለከቱ ብዙ መረጃዎች ተሰርተዋል›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የዳታ ማዕከሉ መረጃዎች እንደሚያ መላከቱት፤ ኢንስቲትዩቱ ዳታ የሚያመነጭ እንደመሆኑ ዳታ ማዕከል እና ልዩ ቤተመጻሕፍት አለው፡፡ ልዩ ቤተመጻሕፍት የተባለው ዋና ምክንያት ከየሀገሪቷ ብቸኛ የሥነ ምድር የተለዩ መረጃዎችን የያዘ ነው፡፡ በሀገሪቷ ከሚገኙ የክልሉ የማዕድን ቢሮዎች፣ በኢንስቲትዩቱም ሆነ በሌሎች አካላት የሚሰበሰበውን መረጃ በማሰባሰብ፣ አደራጅቶ ያሰራጫል፡፡ የዳታ ማዕከሉ መረጃዎችን በሁለት መልኩ በሶፍትና በሀርድ ኮፒ አደራጅቶ ይይዛል፡፡ በሶፍት ኮፒ የተደራጁትን መረጃዎች ተጠቃሚው በቀጥታ /በኦንላይን/ መስጠት እንዲቻል በማድረግ ደንበኞች ወደ ተቋሙ መምጣት ሳይጠበቅባቸው ባሉበት ቦታ ሆነው በኦንላይን የሚፈልጉትን አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ በአሁኑ ወቅት አገልግሎቱን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ነው፡፡

የኦንላይን አገልግሎቱ እስኪጀመር ድረስ ደግሞ ደንበኞችን ለማርካት በኢሜልና በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች የሚፈልጉት መረጃ እንዲያገኙ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። የመረጃዎችን ሀርድ ኮፒ የሚፈልጉ ደንበኞች እንዲሁ ኢንስቲትዩቱ ድረስ በመምጣት ማግኘት የሚችሉ ሲሆን፤ በተለይ ካርታዎች የሚፈልጉ ደንበኞች በአካል ተገኝተው ካርታውን መግዛት እንደሚችሉ አመላክተዋል።

ዳታ ማዕከሉ ለደንበኞች የሚሰጣቸው ዋነኛ መረጃዎች በሥነ ምድር ላይ የተሰበሰቡ ቴክኒካል ሪፖርቶችና ካርታዎች ናቸው፡፡ ዳታ ማዕከሉ ኢንስቲትዩት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ለ56 ዓመታት የተሰበሰቡ በርካታ መረጃዎችን የያዘ እንደመሆኑ ብዙ ዓይነት መረጃዎች አሉት። ከእነዚህም መካከል የጂኦሎጂ፣ የሃይድሮሎጂ፣ የኢንጂነሪንግ፣ የፊዚክስ፣ የተለያዩ በጂኦሎጂ ላይ ተሰሩ እና ሌሎች በርካታ መረጃዎችን መጠቀስ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ በዳታ ማዕከል 18 ሺ የሚጠጉ መረጃዎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህ መረጃዎች በሶፍት ኮፒ እና በሀርድ ኮፒ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡

መረጃዎች በማዕድኑ ዘርፍ ላይ ለተሰማራ ማንኛውም ዓይነት ኢንቬስተር፣ በዘርፉ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ አካላት፣ ከዩኒቨርሲቲዎቹ ለሚመጡ ጂኦሎጂ ተማሪዎች፣ ከውጭ ሀገራት የኢትዮጵያን ጂኦሎጂ ሊያጠኑ ለሚመጡ የውጭ ሀገር ተመራማሪዎች እና ሌሎች መረጃ ፈላጊዎች ይሰጣሉ፡፡ መረጃዎቹ በሁለት ዓይነት መልኩ የሚሰጡ ሲሆን በግዥ እና በነፃ የሚሰጥበት አሰራር ተቀምጧል፡፡ ተማሪዎች ከሆኑ ተማሪ መሆናቸው የሚገልጽ ደብዳቤ ከዩኒቨርሲቲው አጽፈው የሚያመጡ ከሆነ የሚፈልጉትን መረጃ በነፃ የሚያገኙበት አሠራር እንዲኖር ተደርጓል። ከተማሪዎች በስተቀር ማንኛውም መረጃ ፈላጊ የሚፈልገው መረጃ ዓይነት በገንዘቡ ገዝቶ መጠቀም የሚችልበት አሠራር ተዘርግቷል፡፡

በተመሳሳይ የማይፈለጉ ኮንፊደንሻል መረጃዎች (በተለያዩ ምክንያቶች ይፋ እንዳይሆኑ የሚፈለጉ) ይፋ እስኪሆኑ ድረስ ለማንም የማይሰጡና የማይሸጡ ናቸው፡፡ ኮንፊደንሻል የሚባሉ መረጃዎች አንዳንድ ድርጅቶች ማዕድን ፍለጋ ላይ ለመሰማራት ፍቃድ ወሰደው ጥናት ያጠናሉ። ፍለጋው አድርገው ሲጨርሱ በቃን ብለው ወደ ማዕድን ማውጣት ገብተው መረጃው ይፋ እንዲሆን ሲፈልጉ መረጃው ወደዳታ ማዕከሉ ሊገባ ይችላል፡፡ በድርጅቱ እጅ እስካልደረሰና እንዲሰጥ እስካልተፈለገ ድረስ ኮንፊደንሻል ስለሆነ ለማንም አይስጥም፡፡

ዳታ ማዕከሉ እነዚህን አሠራሮች ተከትሎ ሥራዎች ይሰራል፡፡ መረጃዎች ስካን በማድረግ በማተም፣ በሀርድ ያሉትን ወደ ሶፍት በመለወጥ ይሰራል፡፡ በሶፍት ያሉት ደግሞ በሀርድ ኮፒም እንዲቀየር ተደርገው የሚያዙበት አሠራርም ተዘርግቷል፡፡ በዳታ ማዕከሉ ያሉ መረጃዎች በርካታ ቢሆኑም የተወሰኑት ማዕድናት ላይ የተሰሩ መረጃዎችን መመልከት ተገቢ ይሆናል። ለአብነትም ወርቅ ላይ የተሰሩ 267 የሚሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን፤ በብረት ላይ 100 ያህል መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ኮፐር፣ ድንጋይ ከሰል እና የመሳሰሉት ሁሉም ማዕድናት በሚባል ደረጃ መረጃዎች ተሰብስበው እንዲያዙ ተደርጓል።

መረጃዎቹ በሀገሪቷ ላይ ከሁሉም አቅጣጫ የሚሰበሰቡት ሲሆን፤ በተለይ በጂኦሎጂ ካርታዎች ሁሉንም ቦታዎች ማካተት ተችሏል። ኢትዮጵያ በኳርተር ሚሊዮን በ250ሺ እስኬል ማካለል ተችሏል፡፡ አሁን ላይ ደግሞ በጥልቀት በ50 ሺ እስኬል ለመሥራት ሥራው ተጀምሯል፡፡

በኢንስቲትዩቱ በተለያዩ ዘርፎች ያሉ የጂኦሎጂ ባለሙያዎች በየዓመቱ ጥናት የሚያደርጉ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ የጥናቱ ግኝት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ከተገመገመ በኋላ በዳታ ማዕከሉ ባሉ የጂኦሎጂ ባለሙያዎች ታይቶ ሪፖርቱ ተጠናቅቆ የሚቀረብና ወደ ዳታ ማዕከሉ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ የሚቀረው ነገር ካለ ደግሞ በዚህ መልኩ ይስተካከል ሲሉ መልሰው እንዲስተካከል አድርገው የተስተካከለውን ይቀበላሉ፡፡ መረጃው ተደራጅቶ አስፈላጊ ሥራ ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ መረጃውን ለመረጃ ፈላጊዎች ምቹ በሆነ መልኩ አድርጎ በመያዝ በሚፈለግ ወቅት በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል ፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ኢጃራ እንዳብራሩት፤ ኢንስቲትዩቱ የሥነ ምድር ዳታን ያመነጫል ሲባል የተቋሙ ባለሙያዎች በየመስኩ በመገኘት ጥናትና ምርምር ያደርጋሉ፡፡ ናሙናዎች ተሰብስበው ላብራቶሪ ገብተው ትንተና ከተሰራላቸው በኋላ ተገምግሞ ሪፖርቱ ይዘጋጃል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ዘንድሮ የተጀመረው ሥራ ሪፖርቱ በሚቀጥለው ዓመት የሚጠናቀቅ ይሆናል። ምክንያቱም በዘንድሮ ዓመት መስክ ተወጥቶ ናሙናዎች ተሰበሰበው ላብራቶሪ ይገባሉ፤ ከዚያ አስፈላጊውን ሂደት ተጠብቆ ስለሚሰራ ረጅም ጊዜያትን ሊፈጅ ይችላል፡፡

በዚህ ምክንያት አሁን ላይ በዳታ ማዕከሉ ያሉ መረጃዎች እስከ 2015 በጀት ዓመት ድረስ ያሉ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ በመጨረሻም በአሁን ወቅት ወደ ኢንስቲትዩቱ መረጃ ፈልገው የሚመጡ መረጃ ፈላጊዎች የሚፈልጉት መረጃ በሶፍት እና በሀርድ ኮፒ በሚፈልጉት ልክ ተዘጋጅቶ ስላለ በቀላሉ ማግኘት እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ወደ ነገ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዘመን የመቀነስ ስሌት ነው፡፡ ከተሰጠን ላይ አንድ እያጎደለ ወደነገ የሚሰደን፡፡ በአዲስ ዘመን ስም የጣልነው ፍሪዳ፣ የጠመቅነው ጠላ ዋይ ዋያችን ነው፡፡ የጎዘጎዝነው ጉዝጓዝ፣ ያጨስነው ጠጅ ሳር መርዶ ነጋሪዎቻችን ናቸው።

ወደነገ ህይወት የለም..ካለም ከሞት የተረፈ ምናምንቴ ነው፡፡ ግን ከወደትናንት ይሻላል፡፡ የሚመጣው ለሁልጊዜ ካለፈው የተሻለ ነው፡፡ ልዩነቱ ከፊት ሞትና ተስፋ ያደፈጡ መሆናቸው ነው፡፡ ከኋላ እዬዬ ነው..ከጀርባ ባለቀለም ፈሮች ከውይብ ፈለግ ጋር፡፡

የአዲስ አመት ሰሞን ድባብ እንደላጪ ልጅ ቀልብ ነው፡፡ ምላጭ በማይፈሩ እና ብዕር በሚሰጉ ነፍሶች መሀል የሞከከ፡፡ የዘመን ጥባት እንደ እሰይና ዋይ ዋይ በሰርግና ሞት ያጌጠ የእልል እና የውይውይ ቀልብ ነው፡፡

እንኳን አደረሰን እፈራዋለው፡፡ ሞት የሚሉት እርኩስ በሰው ልሳን መልካም ምኞቱን የሚገልጽልኝ እንጂ ሌላም አይመስለኝ፡፡ ባለሁበት እንዳለሁ መቀጠል እንጂ ማንም የዘመን ጥባትን አስታከኮ ሞቴን እንዲነግረኝ አልፈቅድለትም፡፡ ወደነገ ጥጉ እስኪገኝ ሳቄን ካልሆነ እንባዬን ሊያረዳኝ ለሚንጦለጦል ርህራሄ የለኝም፡፡

አዲስ አመት ያለመኖር ጋሻ ጃግሬ ነው፡፡ በአዲስ ስም..በጥባት መልክ ከነገ የሚያኳርፍ፡፡ በእንኳን አደረሳችሁ ስም የመኖርን ጣዕም የሚያመር..የተስፋን አለላ የሚበርዝ፡፡ ባይመጣና ከነክንብንቡ አልፎኝ ቢሄድ ምን ገዶኝ?

በአዲስ አመት ስም ሁሉም ሞቱን እያከበረ ነው፡፡ ከእልል ወደ ስልል..ከእዬዬ ወደ እዬዬ፣ ከአሄሄ ወደ ወይኔ ወደ ወይኔ ወይኔም፡፡

ዝም ብሎ አይኬድም..ከጉም ባተቶ ስር ሰምብቶ እንደሚወጣ የብርሀን ወዝ ሞትም እሰይ እሰይን ተከትሎ የሚመጣ ነው፡፡እንደ ቀይና ጥቁር ሁሉም ማሳሳቻ አለው፡፡ አዋጅ አዋጅ ብሎ የምስራች እንደሚናገር አዋጅ አዋጅ ብሎ ሞታችንን ሊያረዳ በአንድ አፍ ሁለት ምላስ ዘመን አለ፡፡ እናም በዘመን ስም፣ በልደት ፈር በቶርታና በሻምፓኝ ያከበራችሁትና እያከበራችሁት ያለው ሞታችሁን ነው፡፡

‹እንኳን አደረሰህ? ሲሉኝ

‹እንኳን አብሮ አደረሰን› እላለሁ፡፡ ሞትን መጋራት ማለት ይሄ ነው፡፡ በሆነ ውብ ነገር ጀርባ ውበቱን የሚያስከነዳ ማስጠሎነት አለ፡፡ ያ ማስጠሎነት አልታየንም፡፡ ቃሎቻችን እየገደሉን እንደሆነ፣ ልማዶቻችን እያጠፉን እንደሆነ አልገባንም፡፡ ካልገባን ላልገባን ባሪያ ነን፡፡ ከገባን ደግሞ ለገባን አሊቃ ነን፡፡ ከአንድ ውብ የሆነ ነገር ጀርባ ያለው ማስጠሎነት ይሄ ነው፡፡ ዘመን ጺጋ ነው፡፡ መኖር ዋጋ ነው፡፡ የዛሬን ጀምበር ለማየት ናፍቀው ሳያዩ ያለፉ አሉ፡፡ ለዛሬ ጠዋት እቅድ እያላቸው ማታ ከተኙበት ያልተነሱ እንዲሁ ብዙ ናቸው..እንዲህ ባለው ወግ ስር ከዘመን ዘመን መሸጋገር የጺጋ ጺጋ ነው፡፡ ግን በስተጀርባው የሸጎጠውንም ማስጠሎነቱንም ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

ወድጄም ሆነ ፈቅጄ በአዲስ አመት ስም እንኳን ለሞትህ አደረሰህ ሲሉኝ እንኳን ለሞታችን አብሮ አደረሰን ስል እመልሳለሁ፡፡ አዲስ አመት ከዚህ የተለየ ምን ትርጉም አለው? ‹እንኳን አደረሰን እንኳን ለሞትህ አደረሰህ› ውጪ ለይቼ አላየውም፡፡ እንኳን አብሮ አደረሰንን እንኳን ለሞታችን በሰላም አደረሰን ውጪ ትርጉም አልሰጠውም።

ዘመን በጠባ ቁጥር ከእድሜአችን ላይ እየሸረፍን ነው፡፡ ከተሰጠን ላይ እያጎደልን ነው፡፡ ወደአለመኖር እየተጠጋን ነው፡፡ እኔ ዘመን ምኑም አይጥመኝ፡፡ ኪሴን አራቁቶ፣ ጓዳዬን ኦና አድርጎ ከማለፍ በቀር የጠቀመኝ የለም፡፡ ማድጋዬን፣ ገንቦዬን፣ ማሰሮዬን፣ ሌማቴን፣ ድብኝቴን፣ ጎተራዬን፣ ልቤን፣ ህልሜን፣ ተስፋዬን፣ ነገዬን አወይቦ ከማለፍ ሌላ ምን ፈየደልኝ? የተረሱ የባህል ዘፋኞችን ከተረሱ ሙዚቃቸው ጋር አስታውሶ ከማለፍ በስተቀር፣ በእዳና በብድር ነገን እንድሰጋው ከመሆን ባለፈ ምን ቸረኝ? በእከኩ እከካም አደረገኝ እንጂ፡፡ ምኑም አይጥመኝ..ሞትን ከመጥራት ሌላ የዘመን መጥቶ መሄድ ውበቱ አይታየኝም፡፡

ምንድነን? ምንም መሆን ማብቂያችን ከሆነ፣ ከነገ ወደነገ ዝማሜ ፊትለፊታችንን ካሰጋው ምንድነን? እንቁጣጣሽ እንኳን ደህና መጣሽ ባልንበት የሳቅ አፍ እንባ አርቧል፡፡ በጋ ሲሆን እንደተረኛ ክረምት ሳቅ ሲሆን እንባ አለ፡፡ ዘመን በጉያው ሞትን ሸጉጧል፡፡ ከህይወት ሊያጣላን እንቁጣጣሽ በብዙ አብሷል፡፡

ምንድነን? እንባና ሳቅ መላቸው የጠፋን..ፊት ኋላቸው የተሰወረን ሰጋሮች፡፡ ወደነገ ወደህይወት መስሎን..ወደፊት ወደመኖር መስሎን አለመርባትን ያነገስን..ምንድነን?

ዘመን አስልተን፣ እድሜ ቀምረን፣ እለት ቆርጠን በወዳጅ ዘመድ አጀብ በዘመን ስም ሞት ሆይ እንኳን ደህና መጣህ? ማለትን የመሰለ እብደት ታውቁ ይሆን? በሻማና ኬክ ከንቱነትን ማክበር፣ አለመኖርን መዘከር ምን የሚሉት አላዋቂነት ነው?

ትናንት ህይወት..

ዛሬ ህይወትና ሞት..

ነገ አለመኖር..

ከነገ በስቲያ ምንምነት..

ከዛም..

ከዛም..

ከዝም..

ሞትን ግደሉት እንጂ በዜማና ቅኝት፣ በአደይ አበባና በእሰይ እሰይ ቀይ ምንጣፍ አታንጥፉለት፡፡

የሚመጣው እንደሄደው ነው፡፡ የሄደውም እንደሚመጣው፡፡ ከንቱነታችንን ከማስታወስ ባለፈ እቅፍ አበባ ያስታቀፈን ዘመን የለንም፡፡ በመጠበቅ አበባዎቻችን ደርቀዋል፡፡ እንቡጦቻችን ጠውልገዋል፡፡ ተስፋ በማድረግ ሸንቁሮቻችን ሰፍተዋል፣ ጭላንጭሎቻችን ጻልምተዋል፡፡

ሁሉም ትናንት ላይ ነው፡፡ ሁሉም እንደዛሬና ነገ ነው።

ዘመን ማለት ሽርፈት፣ ክሽፈት ነው፡፡ አንድን ማለዳ ለሁልጊዜ መድገም፡፡ የትናንቱን ረፋድና ከሰአት አዲስ ነው ብሎ በአዲስ ስም መቀበል፡፡ ሰኞና ማክሰኞን በተሀድሶ መካደም፡፡ ከነበረ ወደነበረ መሸጋገር ምኑ ነው አዲስ ዘመን? ዛሬ ላይ ትናንትን መድገም፣ ነገ ላይ ዛሬና ከትናንት በስቲያን መቀበል ምኑ ላይ ነው ሽግግር? ከቁጥር ወደቁጥር መተላለፍ የቱ ጋር ነው አዲስነቱ?

የኔ አዲስ ዘመን ዛሬ ነው፡፡ ሞቴን ለሚያስታውስ የዘመን ቆሌ ሳቄን አልገብርም..ደስታዬን አልሸርፍም። ከህይወት ወደህይወት እንጂ ከህይወት ወደሞት አልራመድም፡፡ አሁን ሞት የሌለበት ነጻነቴ ነው፡፡ ከዛሬ ወደነገ እንጂ ከነገ ወደዛሬ ህይወት የለም፡፡ ከአሁን ወደበኋላ እንጂ ከበኋላ ወደአሁን ታሪክ የለም፡፡

ዘመን በአዲስ አመት አጊጦ፣ በአደይና ጻደይ ተሸልሞ በሆታ ሲመጣ ህይወት ያለው ይመስላል.. ከኋላው ጉድፍ አለው፡፡ ዘመን ዘማዊ ነው፡፡ ጊዜ ትካዜ ነው፡፡ ባውካካንባቸው ዘመኖቻችን ላይ እንባዎቻችን ተረኞች ናቸው፡፡ በዘመን ስም ከጥቅል የህይወት ቱባ ላይ መመዘዝ..መተርተር..ምኑ ነው እልል?

በሱፍና ከረባት ሞትን ለህይወት መዳር አይነት ባህል..

ሞት በአካለ ስጋ የመገለጥ ብቃት ቢኖረው አዲስ አመቶቻችንን አብሮን ሲያከብር እናገኘው ነበር፡፡ በልደቶቻችን ቀን ላይ ጥቁር አበባ ሲሰጠን ታዩት ነበር፡፡

# ዓለም አቀፍ

## የተሰደደው ‘ሰላዩ ዓሣ ነባሪ’ ከወታደራዊ ሥልጠና አመለጠ

ከአምስት ዓመት በፊት የቤሉጋ ዝርያ ያለው ዓሣ ነባሪ በኖርዌይ የባሕር ዳርቻ ብቅ ማለቱ መነጋገሪያ ሆኖ ቆይቷል። የአገሬው ሰዎች ነጩን ዓሣ ነባሪ ቫልዲሚር ብለው ሰየሙት። መገናኛ ብዙኃን ደግሞ የሩሲያ ሰላይ ነው በሚል መነጋገሪያ አደረጉት። የዓሣ ነባሪው እንቆቅልሽ አሁን ምላሽ ያገኘ ይመስላል።

አንድ ባለሙያ ዓሣ ነባሪው የጦር አባል ነበር ብለዋል። በዚህም ብቻ ሳያበቁ በአርክቲክ ክበብ ከሚገኝ የባሕር ኃይል ያመለጠ ነው ሲሉ አክለዋል። ዶ/ር ኦልጋ ሽፓክ ግን ሰላይ ነው የሚለውን አያሳምነኝም ይላሉ። ቤሉጋ የሠለጠነው የባሕር ኃይሉን እንዲጠብቅ ነው ብለው ያምናሉ። “አስቸጋሪ” በመሆኑ ሥራውን ጥሎ ሸሽቷል ብለዋል።

ዓሣ ነባሪው በጦር ኃይሏ ስለመሠልጠኑ ሩሲያ አላረጋገጠችም። ተሳስታችኋል ብላም አልካደችም። ዶ/ር ሽፓክ እአአ ከ1990ዎቹ ጀምሮ ሩሲያ ውስጥ አገልግለዋል። በ2022 ወደ ሀገራቸው ዩክሬን እስኪመለሱም ድረስ የባሕር አጥቢዎች ላይ ምርምር ሲያደርጉ ቆይተዋል። “ለእኔ 100 በመቶ እርግጠኛ ነኝ።”

ዶ/ር ሽፓክ ምስክርነታቸውን የሰጡት ሩሲያ ከሚገኙ ጓደኞቻቸው እና ከቀድሞ ባልደረቦቻቸው ጋር ያደረጉት ውይይት ላይ በመመሥረት ነው። ምሥጢራዊው ዓሣ ነባሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ትኩረትን የሳበው ከአምስት ዓመት በፊት ነበር። በኖርዌይ ሰሜናዊ የባሕር ዳርቻ የሚገኙ ዓሣ አስጋሪዎች ካገኙት ጀምሮ መነጋገሪያ ሆነ።

“ዓሣ ነባሪው በጀልባው ላይ መታከክ ጀመረ” ይላል ከዓሣ አስጋሪዎቹ አንዱ የሆነው ጆር ሄስተን። “ጭንቀት የገባቸው እንስሳት ከሰዎች እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው በደመ ነፍስ እንደሚያውቁ ሰምቻለሁ። ይህ አንድ ብልጥ ዓሣ ነባሪ ነው ብዬ



አስቤ ነበር” ሲል አክሏል። ትዕይንቱ ያልተለመደ ነበር። ቤሉጋ ወደ ደቡብ አካባቢ እምብዛም አይታይም። ለካሜራ መሸከሚያ የሚሆን ቀበቶም ታጥቋል። “የሴንት ፒተርስበርግ መሣሪያ” የሚል ጽሑፍ በእንግሊዝኛ ተጽፎበታል።

ሄስተን የካሜራ መሸከሚያውን ለማላቀቅ ረድቶታል። ቀጥሎ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ሃመርፌስት ወደብ ቀዘፈ። በዚያም ለወራት ኖረ። ዶ/ር ሽፓክ ለደኅንነታቸው ሲሉ በሩሲያ የሚገኙትን ምንጮቻቸውን መጥቀስ አልፈለጉም። ቤሉጋ ኖርዌይ ውስጥ ሲታይ የሩሲያ የባሕር ውስጥ አጥቢ እንስሳ ማኅበረሰብ የእነርሱ መሆኑን መለየታቸውን እንደነገሯቸው ገልጸዋል።

“በእንስሳት ሐኪሞች እና በአሠልጣኞች በኩል እንደመጣ መልዕክት ደግሞ አንድሩሃ የሚባል ቤሉጋ ጠፍቷል" ብለዋል። እንደ ዶ/ር ሽፓክ ከሆነ አንድሩሃ/ ቫልዲሚር ለመጀመሪያ ጊዜ የተያዘው እአአ በ2013 በሩሲያ ሩቅ ምሥራቅ በሚገኘው ኦክሆትስክ ባሕር ነበር።

ከአንድ ዓመት በኋላ ደግሞ በሴንት ፒተርስበርግ ወደ ሚገኘው ዶልፊናሪየም (የዓሣ ነባሪዎች ማቆያ) አርክቲክ ወታደራዊ ተቋም ተዛወረ። አሠልጣኞቹ እና የእንስሳት ሐኪሞቹ የሚገኙትም በዚህ ተቋም ነው። “በእንስሳው በመተማመን በክፍት ውሃ ውስጥ መሥራት ሲጀምሩ እንስሳው ተስፋ ቆርጦ እንዳመለጠ አምናለሁ" ብለዋል።

“ከነበረበት ዶልፊናሪየም እንደሰማሁት ከሆነ ዓሣ ነባሪው ብልህ ነው። በዚህ ምክንያት ለሥልጠናም ተመራጭ ሆኗል። በዚያው ልክ ደግሞ ኃይለኛ በመሆኑ ጀልባውን [መከተል] ትቶ ወደ ፈለገበት በመሄዱ አልተገረሙም” ሲሉ ገልጸዋል።

የሳተላይት ምሥሎችን በመጠቀም መርማንስክ የሚገኘው የቀድሞው የቫልዲሚር/አንድሩሃ መኖሪያ የነበረው የሩሲያው የባሕር ኃይል ጣቢያን ለመመልከት ተሞክሯል። በአካባቢው ውሃ ውስጥ ነጭ ዓሣ ነባሪ የሚመስሉ ነገሮች በግልጽ ይታያሉ። “የቤሉጋ ዓሣ ነባሪዎች የሚገኙት ባሕር ሰርጓጅ እና ሌሎች መርከቦች ከሚገኙበት አቅራቢያ መሆኑ የጥበቃ ሥራ አካል መሆናቸውን ሊነግረን ይችላል” ብለዋል።

ቫልዲሚር/አንድሩሃ በሠራዊቷ የሠለጠኑ ናቸው ስለሚባለው ጉዳይ ሩሲያ በይፋ ተናግራ አታውቅም። የባሕር ውስጥ አጥቢ እንስሳትን ለወታደራዊ አገልግሎት የማሠልጠን ግን ረጅም ታሪክ አላት። “ይህን እንስሳ ለስለላ የምንጠቀምበት ከሆነ “እባክዎ በዚህ ቁጥር ይደውሉ” ከሚል መልዕክት ጋር የሞባይል ስልክ ቁጥር የምናያይዝ ይመስላችኋል?” ሲሉ የሩሲያ ተጠባባቂ ኃይል አባል የሆኑት ኮሎኔል ቪክቶር ባራኔትስ እአአ በ2019 ጠይቀዋል።

በሚያሳዝን ሁኔታ ግን የቫልዲሚር/አንድሩሃ አስገራሚ ታሪክ ፍጻሜው አላማረም። እራሱን መመገብን ከተማረ በኋላ በኖርዌይ የባሕር ዳርቻ ወደ ደቡብ በማቅናት ለበርካታ ዓመታት በዚያ አሳልፏል። በግንቦት 2023 ደግሞ በስዊድን የባሕር ዳርቻ ለመታየት በቃ። መስከረም 1 ቀን 2024 ግን አስከሬኑ በኖርዌይ ደቡብ-ምዕራብ የባሕር ዳርቻ ላይ በሪሳቪካ ከተማ አቅራቢያ ባሕር ላይ ሲንሳፈፍ ተገኝቷል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው። እንስሳትን ለስለላ መጠቀም በብዙ ሀገራት እየተለመደ መምጣቱ ይታወቃል፡፡

# በከተማዋ እየሰፋ የመጣው የበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎት

**በኃይሉ አበራ**

በሀገራችንም በተለይ በአዲስ አበባ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተስፋፋ መጥቷል፤ የዚህ አገልግሎት ሀገራዊ ፋይዳም እንዲሁ እያደገ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህን ልምድ ለክልሎች የማካፈል ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

አገልግሎቱ የቆየውን የኢትዮጵያውያን የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባሕል ዳግም እንዲያንሰራራ እያደረገም ይገኛል። በችግር ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች በአገልግሎቱ እየተገነቡ ያሉ መኖሪያ ቤቶች፣ የሚሰጡ የምገባ አገልግሎቶች ፣ የበዓላት ወቅት ማዕድ የማጋራት ተግባሮች የሚያመለክቱትም ይህንኑ ነው፡፡

በዚህ አገልግሎት ወጣቶች፣ ባለሀብቶች፣ ባለሙያዎች ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ። ዜጎች በፈቃደኝነት ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን እውቀታቸውን ለወገናቸው በሚጠቅሙ ሥራዎች ላይ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። ይህን ተከትሎም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ባሕል እንዲጎለብት እንዲጠናከር እየረዳ ይገኛል። መርሃ ግብሩ መንግሥት የዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ለመቅረፍ እንዲሁም ሰላምና ደህንነትን ለማረጋገጥ እያከናወነ ያለውን ተግባር ከጎኑ ሆኖ በመደገፍ እያገለገለ ይገኛል፡፡

በአዲስ አበባ እያደገ የመጣው ይህ አገልግሎት በዚህ የበጋ ወቅትም ቀጥሎ በመዲናዋ አንድ ሚሊየን በጎ ፈቃደኞች የሚሳተፉበት 784 ሺህ 844 ነዋሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የበጎ ፈቃድ ፕሮግራም በርካታ በጎ ፈቃደኞች በተገኙበት ይፋ ተደርጓል።

"በጎ ፈቃደኝነት፤ ለማህበረሰብ ለውጥ!" በሚል መሪ ሃሳብ ይፋ የሆነው ይህ የበጋ በጎ ፈቃድ ፕሮግራም ከጥቅምት ወር 2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ የሚካሄድ ይሆናል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና የበጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን መረጃ እንዳመላከተው፤ የበጋ በጎ ፈቃድ ፕሮግራም በ12 ዋና ዋና ፕሮግራሞች እና በ13 መርሃ ግብሮች ይከናወናል። በእነዚህ መርሀ ግብሮች ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር የሚገመት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዷል። በአገልግሎቱም አንድ ሚሊየን በጎ ፈቃደኞች ሲሳተፉ፤ ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊየን ብር የመንግሥት ወጪን ይታደጋል።

የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን በሚመራው በዚህ አገልግሎት የከተማዋ ነዋሪ ማሬ ሙሉጌታ ላለፉት አምስት ዓመታት ተሳትፎ አድርጋለች፤ በቀጣይም በበጎ ፈቃድ በሚሰሩ ሥራዎች ጊዜዋንና ጉልበቷን ሳትቆጥብ ባላት እውቀት ማህበረሰቡንና ሀገሯን ለማገልገል ዝግጁ ናት።

ደም በመለገስ ሌሎች ወጣቶችንም በማስተባበር እንዲለግሱ በማድረግ፣ የትራፊክ አደጋን ለመከላከል በትራፊክ ማስተናበር ሥራዎች በመሳተፍ እና በማስተባበር ሥራ እንዲሁም በጎነት በሆስፒታል በሚል አቅመ ደካሞችን ተዘዋውሮ የመርዳት ሥራዎች ትሰራለች። በበዓላት ወቅትም ለህብረተሰቡ ማዕድ ማጋራት ላይ ከባለሀብቱ ጋር ከብሎክ ጀምሮ ማህበረሰቡን በማነቃቃት እንዲሳተፉ በማድረግ ላይ የበኩሉን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደምትሰራ ወጣት ማሬ ገልፃለች።


በተለይ በበጎ ፈቃደኝነት በሚገባ ተሳትፎ ያደረገችው ከሶስት ዓመት ወዲህ መሆኑን ጠቅሳ፣ አገልግሎቱ ጊዜን፣ ጉልበትን ሳይቆጥቡ በመስጠት ሰዎችን በፈቃደኝነት በመርዳት የሚከናወን ተግባር ነው ብላለች። ሰዎች ባላቸው እውቀትም ይሁን ጊዜያቸውን በማካፈል አስተባብሮ ከመሥራት እንደሚነሳ ትገልፃለች።

ወጣት ማሬ እንደምትለው፤ መሰል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እና የማስተባበር ሥራዎችን መሥራት ዜጎች ብቻ የሚረዱበት አይደለም፤ በጎ ፈቃደኞች ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም በበጎነት በማገልገላቸው የተነሳ ሀገርም ትጠቀማለች፡፡ የገንዘብ ወጪን በማስቀረት፣ ገንዘቡ ለሌላ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት እንዲውል የሚያስችል በመሆኑ በተዘዋዋሪ ሀገርን መርዳት ነው ብላለች። በበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ዜጎች የሚሰጡት አገልግሎት፣ እንደ መንገድ መሠረተ ልማትና ትምህርት ቤት ያሉትን በመገንባት መንግሥት ለእነዚህ መሠረተ ልማቶች ግንባታ ሊያወጣ የሚችለውን ሀብት እንደ ኮሪደር ልማት ላሉት እንዲያውል በማስቻል ሀገርን የሚያግዝ ሥራ የሚሰራበት መሆኑን ጠቁማለች።

በጎ ፈቃደኛ ወይዘሮ ፀጋ አጪሶ ላለፉት 11 ዓመታት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳትፈዋል፤ በተለይም ባለፉት አምስት ዓመታት በይበልጥ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ወቅት በተለይ የትራፊክ እንቅስቃሴን በማስተናበር ሥራዎች ወቅት ስለበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ግንዛቤ ያልነበራቸው ሰዎች ያጋጥሙ እንደነበር በመጥቀስ፣ ይህም በበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ላይ የተካሄደው ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ሰፊ ክፍተት እንዳለበት መረዳታቸውን ጠቁመዋል።



ወጣት ማሬ ሙሉጌታ፣



ወይዘሮ ፀጋ አጪሶ፣



አቶ ደረጄ ካሳ፣

የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ፣ ልብሳቸውንና ገላቸውን በማጠብ፣ አልባሳትንና መጻሕፍትን በማሰባሰብ ለችግረኞች በመስጠት እንዲሁም በድንበር ተሻጋሪ ሥራዎች እስከ አዳማ፣ ሳውላ እና ሀዋሳ ከተሞች ድረስ ማህበረሰቡን በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማገዝ እና ልምድ ለማካፈል መንቀሳቀሷን አስታውሰዋል።

እንደ ወይዘሮ ፀጋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ መሳተፍ ለሰው ቅን መሆንንና የግል ተነሳሽነትን የሚጠይቅ ነው። በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ወቅት የሚያመሰግኑና የሚመርቁ በመኖራቸው ከደመወዝ በላይ ርካታን ይሰጣል። በተለይ አዛውንቶችን ሁልጊዜ መደገፍ እና ለነሱ መልካም ነገር ማድረግ የሚሰጡት ምርቃት ትልቅ ደስታን የሚፈጥርና አቅም ቢኖር የበለጠ ለመደገፍ የሚያነሳሳ ነው ሲሉ ያብራራሉ።

የአዲስ አበባ የሕብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነርና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያ ዳይሬክተር አቶ ደረጄ ካሳ እንዳስታወቁት፤ ለዘመናት የተከማቹ ችግሮችን እየቀረፈች ዓለም አቀፍ የስበት ማዕከል መሆን በጀመረችው አዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍትህን ለማንገስ የተሰሩ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ፍሬያማ መሆን ችለዋል።

በ2016 ዓ.ም በክረምት በጎ ፈቃድ 5 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የሚገመት አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን ከሦስት ሚሊዮን በላይ በጎ ፈቃደኞች በድግግሞሽ ተሳትፈውበታል። የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር፣ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን በጎ ፈቃደኛ የህብረተሰብ ክፍሎችን በድግግሞሽ ለማሳተፍ ታቅዶ ከሁለት ሚሊየን በላይ ተሳትፎ አድርገዋል። በዚህም በከተማ አቀፍ 20 ሚሊየን እቅድ ታቅዶ ከ26 ሚሊየን በላይ ችግኞች ተተክለዋል። በበጋውም የመንከባከብ ሥራውን የሚከናወን ነው።

በአካባቢ ፅዳት፣ ማስዋብ ላይ እና ከኮሪደር ልማት ሥራው ጋር ተያይዞ ከተለያዩ ባለድርሻዎች ጋር በመሆኑ ከ100 ሺህ በላይ በጎ ፈቃደኞች ተሳትፈዋል። በዚህም ከሁለት ሺህ 996 ሜትሪክ ቶን በላይ ቆሻሻ ለማንሳት ተችሏል።

በደም ልገሳም ቋንቋን ፆታን ሳይለይ ከ32 ሺህ 600 በላይ ወጣቶች ደም ለግሰዋል። ይህም አንድም እናት በወሊድ መሞት የለባትም በሚለው መርህ አርአያነት ያለው የበጎነት ተግባር ነው። “በጎነት በሆስፒታል” በሚለው መርሃ ግብርም ህሙማንን የመንከባከብ፣ የመጠየቅ ተግባራት ተከናውነዋል።

የትራፊክ በጎ ፈቃደኞች በማስተባበሪያው መሳተፋቸውን አስታውሰዋል። በተመሳሳይ “ሙያዬ በሀገሬ” በሚል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሙያን መሠረት ያደረጉ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች በተለይ የህክምና ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ የስፖርት ባለሙያዎች በሙያቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሰጡበት መድረክ ተፈጥሯል።

በከተማ ግብርና፣ በከተማዋ ሰላም በጎ ፈቃደኞች አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በድንበር ተሻጋሪ ሥራዎች ከከተማዋ ወጣ በማለት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ውጤታማ ሥራ ተሰርቷል፤ የሕዝብ የእርስ በርስ እሴት በማዳበር ትውውቅ በማጠናከር ፕሮግራሞች ተከናውነዋል።

በዚህም በአዲስ አበባ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተከናወነ የሚገኝበትን ሁኔታ ተሞክሮ በማጋራት አርአያነትን የማስፋት ሥራዎች የተሰሩ መሆናቸውንም አስረድተዋል። በዚህም በወሰን የለሽ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከሁለት ሺህ 220 በላይ በጎ ፈቃደኞችን ማሳተፍ ተችሏል። በእነዚህ ተግባራት አጠቃላይ ክንውን ተሳታፊ የነበሩ አካላት እና ባለሀብቶች ጳጉሜን አራት 2016 ዓ.ም በከተማ አስተዳደሩ እና በየደረጃ እውቅና እና ምስጋና መሰጠቱን አስታውሰዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በጎ ፈቃድ አገልግሎት በዘላቂ ልማት ያለውን አስተዋጽኦ ማሳደግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት፣ ተሳትፎ ማጠናከር ላይ በአጠቃላይ ከ764 ሺህ በላይ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስታውቀዋል። ከእነዚህ አንዱ ማዕድ ማጋራት ሲሆን፣ በዚህም ዘላቂ ችግሮችን ለመፍታት አብነትን ለማሳየት፣ በስፋት እየተከናወነ ነው።

በቤት እድሳት እና ግንባታ በአራት እና ሶስት ወራት 25ሺ 74 ቤቶች ተገንብተዋል። ከዚህ ውስጥ 812 በከፊል ከ17ሺህ 62 በአዲስ መልኩ ከጂ ፕላስ በላይ የተገነቡ ናቸው። በቤተሰብ ደረጃ ከ14 ሺህ በላይ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። ይሄም በተለይም በደሳሳ ጎጆዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ያደረገ ነው።

ከነፃ ህክምና ጋር ተያይዞ ከፍለው መታከም የማይችሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማገዝ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ የጤና ተቋማት የተሳተፉበት ከ89 ሺህ በላይ ሰዎች ተጠቃሚ ሆነዋል ሲሉም ጠቅሰው፣ ይህም መስፋፋት እንደሚገባው ጠቁመዋል። ቀደም ሲል ከውጭ ባለሙያዎች ወደ ሀገራችን መጥተው ይህንን ተግባራዊ ሲያደርጉ እንደነበር አስታውሰው፣ የሀገራችን ባለሙያዎች የበጎ ፈቃድ የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ አቀናጅቶ ማስተባበር ማስፈለጉን ጠቁመዋል። በማጠናከሪያ ትምህርት፣ በጎልማሶች፣ በአጫጭር ትምህርት ተግባራት ከትምህርት ቢሮ ጋር በመቀናጀት ከ94 ሺህ በላይ ተማሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

እንደ አጠቃላይ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራው በእውቀት፣ በጉልበት በሙያ የተሰጡ አገልግሎቶች ወደ ገንዘብ ሲቀየሩ ከአምስት ነጥብ አራት ቢሊየን ብር በላይ የመንግሥትን ወጪ የመቀነስ አስተዋጽኦ መደረጋቸውን አስታውቀዋል። ከእነዚህም መካከል በቤት ግንባታ ከሁለት ነጥብ ሶስት ቢሊየን ብር በላይ አስተዋጽኦ መደረጉን አመላክተዋል። ለእዚህ ውጤት መገኘት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳትፎ የጎላ ሚና ነበረው ሲሉም ምስጋና አቅርበዋል።

አቶ ደረጄ እንደሚናገሩት፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያው የትኛውም ዜጋ ያለማንም አስገዳጅነት ገንዘቡን፣ እውቀቱን፣ አቅሙን ጊዜውን ለማህበረሰቡ በሚጠቅሙ ተግባራት በራሱ መልካም ፈቃድ ያለ ክፍያ የሚሳተፍበት ነው። ይህን በማድረጉ ሀገርን ከማገዙ ባሻገር የህሊና እርካታ ያገኝበታል። ማስተባበሪያው ለበጎ ፈቃደኞች የአገልግሎት አሰጣጥ የማስተባበር ሁኔታዎችን ያስተባብራል።

የመዲናዋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በተቋም መመራት ከጀመረ ባለፉት ስድስት ዓመታት በርካታ ውጤታማ ተግባራት ተከናውነዋል። የህብረተሰቡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትና ግንዛቤ እያደገ መምጣቱ፣ ባለሀብቶች፣ በጎ ፈቃደኞች በስፋት በመሣተፍ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እያደረጉ ናቸው። በተለይ በማዕድ ማጋራት፣ በቤት ግንባታና እድሳት፣ እየተሳተፉ የማህበረሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እየቀረፉ ናቸው። ተሳትፎውም ጨምሯል ብለዋል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባራትና መርሀ ግብሮች በጥራትም በቁጥርም እየበዙ በተለያዩ መስኮች ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እያደረጉ ናቸው። በገንዘብ ደረጃም በጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይም የሚውለው ገንዘብ እያደገ ነው። የከተማ ቤት ግንባታዎች እይታ ከመቀየር አኳያም ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆን ተችሏል።

በጥቅሉም የህብረተሰቡን የመረዳዳት፣ የመተጋገዝ ባሕልን ማጠናከር ላይ፤ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር በኢኮኖሚያዊ ዘርፉ ላይ ተሰርቷል። የከተማዋን ሰላም በማስፈን የበጎ ፈቃደኞች ተሳትፎ ከፍተኛ ነበር። በማህበራዊ ሆነ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፉ ለውጥ ማምጣት መቻሉን አስገንዝበዋል። በዚህ የደረሰን የበጎ ፈቃደኞች ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ እንደ ተቋም የበጎ ፈቃድ የሚሰጡትን እንደ ድልድይ ሆኖ የማስተባበር፣ ባሕል እንዲሆን፣ እንዲጎለብት፣ እንዲጠናከር፣ ልምምድ እንዲደረግ እየተከናወነ ያለው ተግባር የታዳጊ ወጣቶች ስብዕና እንዲገነባ፣ በራስ መተማመናቸው እንዲጨምር ያግዛል።

በዚህ ሂደት ክፍያ የሚባለው ለምሳሌ ለአንድ በጎ ፈቃደኛ ከአንድ አካባቢ በራሱ ትራንስፖርት ተንቀሳቅሶ እንደ ምሳ ላሉ ገንዘብ ያወጣል። ለዚያች የተወሰኑ ወጪ መተኪያዎች ሊደረግለት ይችላል። ከዚያ ባለፈ ማስተባበሪያው በጎ ፈቃደኞች ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውን እና ጉልበታቸውን ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲያውሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ላይ እንደ ድልድይ ሆኖ የማገልገል ሥራ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ ግለሰቦችና ተቋማት አሉ፤ በተመሣሣይ ደግሞ በበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ አዛውንት እና አረጋውያን በመኖራቸው ድልድይ ሆኖ ማገናኘት እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግራቸው እንዲቀረፍ የማስተባበር ሥራን ይሠራል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር ይመር ከበደ በበኩላቸው በጎ ፈቃደኝነት መንግሥት ተደራሽ ያላደረጋቸውን ተግባራት በመከወን በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን እየፈታ መሆኑን ገልጸዋል። በከተማዋ በ2016 በጀት ዓመት ከ12 ቢሊዮን ብር በላይ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠትና የበርካታ ነዋሪዎችን ተስፋ ያለመለመ ፕሮግራም በመተግበር ለሀገራችን ከተሞች በምሳሌነት የሚጠቀስ ሥራ ተሰርቷል ሲሉ ጠቅሰዋል።

በበጋ የበጎ ፈቃድ ሥራዎችም ችግኞችን በመንከባከብ፣ በሰላም እሴት ግንባታ፣ ለችግር የተጋለጡ ወገኖችን በመደገፍና ማገዝ ተገቢ መሆኑን ገልጸዋል። በጎ ፈቃደኞች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት በተለመደው ቅንነትና ታታሪነት ማህበረሰቡን እንዲያገለግሉ ጠይቀዋል። በበጋው የተያዘው ፕሮግራም ውጤታማ እንዲሆን ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥሪ አቅርበዋል።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

## ለጦርነት የበረታነውን ያህል ለሰላም እንበርታ!

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሸክታብ)

ስለኢትዮጵያ በጋራ ለጋራ የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ከትላንት የተመዘዘ፣ ዛሬም የቀጠለ ለነገም ዋስትና የሚሆን ከብዙኃነት ለብዙኃነት ዓይነት ዘውግ ያለው ሃሳብ መሆኑ ሲያስማማን ከጥቅምና ከመሰል የጋርዮሽ መስተጋብሮች አኳያ ሲታይም እጅግ ዋጋ ያለው፣ በላጭና አዋጭ ሆኖ እናገኘዋለን:: ለነበሩብንና ለሚኖሩብን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች አስታራቂ ምላሽ በመስጠት ስለሰላም አቻ የለሾች ናቸው::

ስለኢትዮጵያ በጋራ ለጋራ በትልቁ የሚነሳ ሰፊና ገናና መልዕክት ያለው ሃሳብ ነው። በተለይ አሁን ላለንበት የፖለቲካ ሽኩቻ፣ በተለይ በዘርና በጎጥ ለተቧደነው ትውልድ፣ በተለይ ኢትዮጵያዊነት ለጠፋበት አእምሮ፣ ጦርነትን እንደዋነኛ የመፍትሔ አማራጭ ለወሰደው ፖለቲከኛ፣ በሀሰት ትርክት የጥላቻ መርዝ እየረጩ ላሉ መልስ የሚሰጥ ነው::

ኢትዮጵያዊነት እጅግ በጣም በሚል አጋዥ ቃል ካልተገለጠ በቂ ሊሆን የማይችል የብዙኃነት ስም ነው:: የዛሬን አያድርገውና በዓለም አደባባይ ስም ባሰጡን የነፃነትና የሰላም፣ የፍትህና የሰብዓዊነት ስሞች ተጠርተናል:: እኚህ ስሞች እንዴት መጡ ብሎ የጠየቀ ለጋራ በጋራ በተማጠ ሃሳብና ትስስር እንደመጡ መረዳት ይችላል:: አሁናዊ ዘር ተኮር እሳቤዎች፣ የሰላምና መሰል ጥያቄዎች እንዴት ተወለዱ ላለም በጋራ ለጋራ ትስስራችንን በማላለት የፈጠርናቸው እንደሆኑ ለመረዳት አይቸግረውም::

በጋርዮሽ ውስጥ ስላለው ጸጋና በረከት፣ አንድነትና ሉዓላዊነት፣ ክብርና ከፍታ ከእኛ በተሻለ የሚያውቅ የለም:: ታሪክ የከተቡ ዳናዎቻችን በዚህ ቀለም ተውበው ኢትዮጵያዊነትን የፈጠሩ ስለመሆናቸው ተጠራጣሪ ባይኖርም አሁን ላይ ስለወየቡበት ምክንያት ግን መልስ የሌለን መሆናችን በራሱ ትልቅ ጥያቄ ሆኖ የሚነሳ ጉዳይ ነው:: በጋራ ለጋራ ጽንሰ ሃሳብም ይሄን ድብዛዜ በማድመቅ ወደመጣንበት ጥንተ ጠዋታችን በመመለስ ኢትዮጵያዊነትን የማስቀጠል ንቅናቄ ነው::

ሀገር እንደ አንዲት ጉብል ብትዘከር ስሜት ያላት፣ ራዕይና ህልም የነበራት፣ ጥላቻና መለያየት የሚያስጨንቋት፣ ዘረኝነትና ቡዳኔ ክብሯን የሚገልቡባት ብለን ልንገልጻት እንችላለን:: ይሄ ገለጻ ኢትዮጵያ ድሮና ዘንድሮ በሚል መታየት የሚችልም ነው:: ሀገር ስሜት የሌላት የሚመስለን ካለን ስህተተኞች ነን:: ሀገር ስሜት አላት:: ምንም እንኳን በግዑዝ የምትጠራ ብትሆንም የዜጎቿን ስሜት በማስተጋባት በቀዳሚነት የምትጠራም ናት:: ለዛም ነው ሀገራችን ስትነካ የምናነባው:: ለዛም እኮ ነው ለሀገር በተዜሙ ዜማዎች ትካዜ ውስጥ የምንወድቀው::

ነፃነቶቻችን ክብሮቻችን እንደሆኑ አሁናዊ ንትርኮቻችንም ስቃዮቻችን ናቸው። አስታራቂነታችን መጠሪያዎቻችን እንደነበሩ አሁናዊ የእርስ በርስ መገዳደላችንም ውርደቶቻችን ናቸው:: አሸናፊ በሌለው በእኔና በእናንተ ትግል ኢትዮጵያ ከክብሯ ትጎላለች:: ብኩርና በሌለው የወንድማማችነት ግፊያ ሀገራችን ክብረ ንጽህናዋ ያድፋል:: ቀዳሚ በሌለው የእርስበርስ እሽቅድምድም አብሮነታችንን እያወደምን ነው:: በእልህና ባለመደማመጥ ሀገር ጠባቂ መሆናችን ቀርቶ ሀገር ደፋሪዎች እየሆንን ነው:: ይሄ ዓይነቱ አካሄድ እንዲረግብ ስለሀገራችን በጋራ ለጋራ ልንወያይ፣ ልንመካከር ይገባል:: ያጠፋ ተረክዝ እንዲይዝ፣ የተበደለ በካሳ እንዲሽር ቢደረግ መልካም ይሆናል::

ሌላው ሀገር ከእኛ ባነሰ የእርቅና የሉዓላዊነት አረዳድ ሀገር ሰርቷል:: ከእኛ ባነሰ ሥልጣኔና ዘመናዊነት ታሪክ ሰርቷል፣ እሴት ገንብቷል:: ከእኛ ባነሰ ሕዝባዊ ትስስር ሥርዓት ሰርቷል፣ በፍቅር የሚመራ ትውልድ አንጿል:: ፊት ተፈጥረን የእኛ ወደ ኋላ ማለት የሚያስቆጭ ቢሆንም ለተሃድሶ ከተነሳን ግን አሁንም ቢሆን ጊዜ እንዳለን ማወቅ ይቻላል:: የሀገሩን ክብረንጽህና ጠብቆ በስሟ ስም አግኝቶ እንዲኖረው እንደዛኛው ትውልድ ልዩነቶቻችንን በእርቅ በመቅጨት በጦርነት ክብሯን ያጣች ሀገራችንን መካስ እንችላለን::

**በአክሳሪ ጦርነት ስድስት አስርት ዓመታትን መጓዝ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ዓለም አቀፍ የሰላም ስም ላላቸው ሀገራት ከፍተኛ ውርደት ነው:: ይሄ ዘመን ያለፉ አክሳሪና ጥቅም አልባ ጦርነቶችን እየጠቀስን ስለሰላም አስፈላጊነት የምንናገርበት እንጂ አዲስ ጦርነት ከፍተን መከራ የምናይበት አይደለም**

በአክሳሪ ጦርነት ስድስት አስርት ዓመታትን መጓዝ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ዓለም አቀፍ የሰላም ስም ላላቸው ሀገራት ከፍተኛ ውርደት ነው:: ይሄ ዘመን ያለፉ አክሳሪና ጥቅም አልባ ጦርነቶችን እየጠቀስን ስለሰላም አስፈላጊነት የምንናገርበት እንጂ አዲስ ጦርነት ከፍተን መከራ የምናይበት አይደለም:: ሌላው ዓለም ንቆና ገፍቶ የተዋቸው የዘረኝነት እሳቤዎች እኛ ሀገር የመዘመናቸው ነገር ያስቆጫል:: በሰባና በሰማኒያ ዘመን ለተመተረ እድሜያችን ፍቅር ሰጥተን ፍቅር ብንቀበል፣ ትውልዱን በሀቅ ምንጣፍ ላይ ብናራምድ ምን እናጣለን::

ሀገር ግን ለሁልጊዜ በዜጎቿ ትከሻ ላይ ናት። እንደ ሰው ከአስራ ስምንት ዓመት በኋላ የራሷ ኃላፊነት ነው የምትባል አይደለችም:: በሕዝቦቿ ምክር እና መርገምት የምትለማና የምትከስር ሆና የምትኖር ናት:: ለዛም ነው በሃሳብ ሀገር ስለመገንባት አብዝተን የምናወራው። ዜጎች ሃሳብ ከሌላቸው ሀገር በምግብ እጦት እንደቀነጨረ ሕፃን ልጅ ናት:: ለሰው ምግብ ለሀገር ደግሞ ሃሳብ እጅግ ወሳኝ ነገሮች ናቸው:: የእርቅና የስምምነት ሃሳብ ስላጣን ነው ስልሳ ዓመታትን በጦርነት የሰነበትነው። የከሸፍንባቸው እነዛ ስልሳ ዓመታት ለእኛ የውድቀት ለታናናሾቻችን ደግሞ የከፍታ ዘመን ሆነው አልፈዋል::

ስለኢትዮጵያ በጋራ ለጋራ ሲባል፤ ከላይ ለዘረዘርኳቸው እንከኖቻችን የመፍትሔ አማራጭ እንዲሆኑ፣ ሰላምን በጦርነት ውስጥ ከመፈለግ ወጥተን በሃሳብ የበላይነት ችግሮቻችንን ድል እንድንነሳ በማሰብ ነው:: አዲስ ነገር የለንም... አሁን ላይ አዲስ ነገሮቻችን አልቀዋል:: ስለሰላምና ዋጋው አውርተናል። ስለጦርነት አስከፊነት ብዙ ዘክረናል:: ስለአንድነትና ወንድማማችነት ብዙ ጽፈናል። ስለኢትዮጵያዊነት እልፍ ጊዜ ለምክክር ተቀምጠናል:: ያቃተን ተግባር ነው:: ለውጥ ያለተግባር ደግሞ ከንቱ ነው::

ዓለም ብዙ ድንቅ አስተምህሮቶች አሏት። ከዛ ውስጥ አንዱ ለውጥ ከተግባር ጋር የተቃቀፉበት አስተምህሮ ነው:: የጦርነት አስከፊነትን እያወቅን ሰላምን ጦርነት ውስጥ ከፈለግን፣ የወንድማማችነትን አስፈላጊነት እየተረዳን ስለዘረኝነት ከደከምን ራሳችንን በብርቱ መፈተሽ ያስፈልጋል:: አሁን ባለው ሁኔታ እየሆኑብን ላሉ ማናቸውም ነገሮች ተጠያቂ ራሳችን ነን:: ለጦርነት የበረታነውን ያህል ለሰላም መበርታት አለብን::

ልማድ ክፉ እንደሆነ ዓለም ሌላም አስተምህሮ አላት:: ከሰይጣን የበረታ አንድ እውነት በምድር ላይ ቢኖር ክፉ አመል ነው። ሰይጣንን በስመአብ ብለን እናባርረዋለን ክፉ አመል ግን በቀላል እንዳይተወን ሆኖ የተጣበቀን ነው:: የሀገራችን የጦርነት አባዜም ከዚህ ክፉ ልማድ ጋር የሚያያዝ ነው:: የሚበልጠውን መከተል ያስፈልጋል:: ሀገር የሁላችንም ቀዳሚ ጉዳያችን ናት:: በሰላም ካልሆነ በጦርነት ልናስከብራት አንችልም:: ልምዶቻችን ዋጋ እያስከፈሉን ከሆነ ቆም ብሎ በማሰብ የሰላም አማራጮችን ማጤን ያስፈልጋል:: 60 ዓመት ተዋግተን ትርፍ ካላመጣን የጦርነት ጥቅሙ ምንድነው? ስንል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው::

ከግጭት ወደ ሃሳብ ፍጭት የሚደረግ አዲስ የሰላም አቅጣጫ የዚህ ጽሑፍ አበይት ጉዳይ ሆኖ የሚነሳ ነው:: የመጣንበትን ባለመድገምም አዲስ የእርቅ ጎዳና በመቅደድ ልማዶቻችንን ለማስወገድ ጥረት ማድረግ አለብን:: ሀገር የጋራ ርስታችን ናት:: በጋራ ርስት ላይ ደግሞ የብቻ ሃሳብ፣ የብቻ እቅድ የለም። የጋራ ርስት የጋራ ሃሳብ፣ የጋራ ባሕል፣ የጋራ ሥርዓት የተባው እውነት ነው:: አጉል ትርክት ለመፍጠር ካልሆነ በዚህ አብሮነት መሀል የሚነሳ ማንኛውም ነገር ትርጉም አይሰጥም::

አሁን ያለው ሀገራዊ ሁኔታ ስለኢትዮጵያ ዝም ባለማለት፣ ስለሰላሟ አስታራቂ ሃሳቦችን በማንሳት የበኩላችንን እንድንወጣ የሚያስገድድ ነው:: በያገባኝም መንፈስ ከዳር ቆመን የምንመለከተው ሳይሆን በየሙያችን ሰላም ሰባኪ፣ አንድነትን ዘካሪ በሆኑ በጎ ንግግሮች እንደአስታራቂ በመሆን የበኩላችንን የምንወጣበት ጊዜ ነው:: ጊዜያቸውን ያልጠበቁ ዝምታዎች ዋጋ አስከፍለውናል:: ጊዜው የራሳችንን ጠጠር የምናስቀምጥበት እንጂ በምንቸገረኝ ዝም የምንልበት አይደለም::

በጋራ ለጋራ በሚል ሃሳብ መነሳቴ በብዙ ምክንያት ቢሆንም እንደዋነኛ የሚነሳው ግን ጥልን በፍቅር መሻር ላይ ነው:: ጥልን በፍቅር የሚሽር ትውልድ ምንሽሩ ኢትዮጵያዊነት ነው። ጦርነትን በሰላም የሻረ ፖለቲከኛ አላማው ሀገርና ሕዝብ ነው:: ከግል ፍላጎት መንጭተው የሚፈሱ ወንዞች የሆነ ጊዜ ውቅያኖስ ሆነው ሀገር ማስመጣቸው አይቀርም:: ሀገር ከመስመጧ በፊት በጋራ ለጋራ መኖርን እንለማመድ:: ከአንድ ወገን በተነሳ ማዕበል ታሪክ ከተበላሸና ሀገር ከሰመጠች በኋላ ለሰላም የምንቀመጠውን ነባር ልምምድ ትተን ከማዕበሉ በፊት የሚነሱ ገባር ወንዞችን በሰላማዊ ማድረቅ ላይ እናተኩር።

በድህነትና በኋላ ቀርነት እየተጠራን በጦርነት ወደባሰ አዘቅት መውረድ እጅግ አሳፋሪ ነው። ሰማይ እንኳን በደመና ይሻራል:: በጋ እንኳን በክረምት ይረታል:: ጸደይ በመኸር፣ በልግ በሆነ ወቅት ያበቃል:: የእኛ ከጦርነት መውጪያ ዘመን መች ነው ? በደም አጊጠን ደመኛ መባል ውበቱ ምኑ ነው? በወንድም ሞት ጀግኖ ኒሻን ማጥለቅ ምኑ ነው ዝማኔው ? በጋራ ለጋራ ደከምን እንጂ መቼ ለብቻ ኖረን? ከብዙኃነት ለብዙኃነት የወገነ፣ ነጣጣይ ትርክቶችን በመሻር የእርቅና የስምምነት አማራጮችን የሚከፍት የትውልዱ የተሃድሶ አቅጣጫ እስከመሆን የሚደርስ የመከባበር መንፈስ ነው::

ከእርስ በርስ በተወጣጣ ባሕልና ወግ የዳበሩ፣ በምንም እንዳይላሉ የጠበቁ፣ በደምና የተሳሰሩ የትስስር ገመዶች ቋጠሯቸውን ሰውረው ኢትዮጵያዊነትን እንዲያስቀጥሉ እንዲህ ያሉ የሰላም ቃሎች ዋጋቸው የት የሌለ ነው:: አሁን ባለው ሀገራዊ ሁኔታ የሚፈለገውን ሕዝባዊ ሰላም ከማምጣትና የፖለቲካ ምህዳሩን ከማስፋት ረገድ ቢታዩም አዋጪ የሚሆኑ ናቸው:: አብረን በቅለን በኢትዮጵያዊነት ተነስተን ሰውና ባለታሪክ የሆነበት ያ ማለዳ፣ ያ ረፋድ የከሰዓትና አመሻሽ በኩር ሳቄ ናፍቆቴ ነው::

በጋራ መንጭተው ለጋራ የቆሙ በመልካም እሴት የሚጠሩ፣ ከሕዝብ ተመዘው ሕዝብን እያገለገሉ ያሉ የኢትዮጵያዊነት ጽንሰ ሃሳብ አቀንቃኝ እውነታዎች አሉን:: በሥርዓት ተገርተው ነውረኝነትን የሻሩ፣ እኛነትን ያስቀጠሉ ለአብሮነት የወገኑ የወንድማማችነት አክሊሎች ያስፈልጉናል:: ሞት የሌለበት፣ ዘረኝነት የመከነበት ስለአብሮነት ቃልኪዳን የምንገባበት ከሁላችን ለሁላችን የሚሆን አስተሳሰብ፤ ጦርነትን በነበር ትተን በምክክር የጸናች ሰላማዊ ሀገር የምናዋልድበት የሰላም ምኩራብ ያስፈልገናል::

# ስፖርት





## የዋልያዎቹን የአፍሪካ ዋንጫ ተስፋ የሚወስነው ፍልሚያ

ዓስማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የ25 አፍሪካ ዋንጫ ሁለት ቀሪ የምድብ ጨዋታዎቹን ከታንዛኒያና ዲሞክራቲክ ኮንጎ ብሔራዊ ቡድኖች ጋር በቀናት ልዩነት ያካሂዳል፡፡ ዋልያዎቹ ባለፉት አራት የማጣሪያ ጨዋታዎች አንድ ነጥብ ብቻ መሰብሰብ ቢችሉም ወደ 2025ቱ የአፍሪካ ዋንጫ ለመመለስ ተስፋቸው ሙሉ በሙሉ አልተሟጠጠም፡፡ ከታንዛኒያና ከዲሞክራቲክ ኮንጎ ጋር የሚያደርጋቸው ሁለት ቀሪ የማጣሪያ ጨዋታዎች ውጤት የአፍሪካ ዋንጫ ተስፋቸውን የሚወስኑ ይሆናል፡፡ የዋልያዎቹ ወደ አፍሪካ ዋንጫ መመለስ ተስፋ በምድብ ማጣሪያው የሌሎች ሀገራት ውጤት ላይ የተንጠለጠለ ቢሆንም፣ ቀሪዎቹን ጨዋታዎች የግድ ማሸነፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህ ሁለት ጨዋታዎች ሙሉ ነጥብ ማግኘት ካልቻሉ የአፍሪካ ዋንጫ ተስፋቸው ያበቃል፡፡

ብሔራዊ ቡድኑ ለሚያደርጋቸው ሁለቱ የመጨረሻ ጨዋታዎች 10 ሚሊዮን ብር ወጪ እንደሚደረግ ፌዴሬሽኑ ከትናንት በስቲያ በሰጠው መግለጫ አስታውቋል፡፡ ብሔራዊ ቡድኑ የምድቡን አምስተኛ ጨዋታ ነገ ከታንዛኒያ እንዲሁም ስድስተኛና የመጨረሻ ጨዋታውን ከዲሞክራቲክ ኮንጎ ጋር ማክሰኞ ያከናውናል፡፡ ሁለቱም የምድቡ የመጨረሻ ጨዋታዎች በዲሞክራቲክ ኮንጎ ሜዳ የሚካሄዱ ሲሆን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ለማካሄድ እንደተወሰነ ተገልጿል፡፡

ከታንዛኒያ ጋር የሚደረገውን ጨዋታ ኢትዮጵያ በሜዳዋ የምታደርግ ቢሆንም፣ የካፍንና የፊፋን ደረጃ የሚያሟላ ሜዳ ስለሌላት እና የመጨረሻው የማጣሪያ ጨዋታ በኮንጎ ሜዳ በመሆኑ ሁለቱንም ጨዋታዎች እዛው ለማድረግ መወሰኑን ፌዴሬሽኑ አሳውቋል፡፡ ጨዋታዎቹን በአንድ ቦታ ለማካሄድም ከ9 እስከ 10 ሚሊዮን ብር ወጪ እንደሚያደርግም ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ባህሩ ጥላሁን፣ የብሔራዊ ቡድኑ ጊዜያዊ ዋና አሰልጣኝ መሳይ ተፈሪ ቀሪ የአፍሪካ ዋንጫ ጨዋታዎችን እና የቻን ማጣሪያ ጨዋታዎችን እንደሚመሩ በፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈጻሚ



ዋልያዎቹ የሀገር ውስጥ ዝግጅታቸውን ጨርሰው ትናንት ወደ ኪንሻሳ ተጉዘዋል፣

ኮሚቴ ውሳኔ መተላለፉን አስታውሰው፤ አምስተኛና ስድስተኛ የማጣርያ ጨዋታዎች በኮንጎ ኪንሻሳ እንደሚደረጉ ጠቁመዋል።

የካፍና የፊፋን ደረጃ ማሟላት የሚችል ስታድየም ባለመኖሩ ምክንያት፣ በሜዳ መካሄድ የሚኖርባቸው ጨዋታዎች ከሀገር ውጪ እየተካሄዱ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ይህም የሆነው በአንድ ጉዞ ሁለት ጨዋታዎችን ለማድረግና ወጪ ቆጣቢ የሆነ መንገድን ለመከተል ታስቦ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ ነገ ከታንዛኒያ ብሔራዊ ቡድን አስተናጋጅ ሆና አምስተኛና የሜዳዋን ጨዋታ ታከናውናለች፡፡

በአፍሪካ ዋንጫና ዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች ብሔራዊ ቡድኑ በሜዳው ማድረግ የሚገባውን ጨዋታዎች ከሜዳው ውጪ እያደረገ በመሆኑ ፌዴሬሽኑ እንደ ተቋም ዋጋ እየከፈለ እንደሚገኝ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገልጸዋል፡፡ ቡድኑ የአንድ ጨዋታ ጉዞ ለማድረግ ከፍተኛ ገንዘብና ቁሳቁስን እንዲሁም ጨዋታን በሌላ ሀገር ከማስተናገድ ጋር ፈታኝ እንደሆነበት አቶ ባህሩ አስረድተዋል፡፡ በዚህም ለጨዋታና ጉዞዎች የሚወጡት ወጪዎችን ለመደጎም ታስቦ፣ የተለያዩ ማስታወቂያዎች ይሰራሉ፡፡ ከነዚህም መካከል የሜዳ ዳር ማስታወቂያዎች የሚጠቀሱ ሲሆን እነዚህም ማስታወቂያዎች ብዙ ከሆኑ ፌዴሬሽኑ የሚያገኘው ገቢ ከፍ ሊል እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡ለዚህም ከእግር ኳስ ውርርድ ድርጅቶች ጋር አብረው እየሰሩ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ባህሩ፣ ባህልንና ማንነትን የሚፈታተኑ ነገሮችን እንደማይኖሩና ለፌዴሬሽኑ ገንዘቡ እጅጉን አስፈላጊ ስለሆነ አብሮ ለመስራት መወሰኑን አመላክተዋል፡፡

የታንዛኒያን ጨዋታ እዛው ጎረቤት ሀገራት ሜዳ ማድረግ ይቻል እንደነበር ጠቅሰው፤ ከኮንጎ ጋር መጨረሻ ጨዋታ በመኖሩ ሁለቱንም ጨዋታዎች በአንድ የአየር ትኬት ለመጠቀምና ወጪ ለመቀነስ ታስቦ እንደሆነም አስረድተዋል። በመሆኑም ሁለቱን ጨዋታዎች ለማድረግ ከ 9 እስከ 10 ሚሊዮን ብር ፌዴሬሽኑ እንደሚያወጣ ጠቁመዋል፡፡ በዚህም መሰረት ፌዴሬሽኑ ከፊፋ፣ ካፍና ከስፖንሰር በሚያገኛቸው ገቢዎች እየተንገዳገደ እስከ አሁን መጓዙን የሚጠቁሙት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ ብሔራዊ ቡድኑ በገንዘብ የማይደገፍ ከሆነ በቀጣይ አዳጋች እንደሆነም አሳስበዋል፡፡ ከችግሩ መውጫ የሆነ እቅድ በፌዴሬሽኑ እየተዘጋጀ ሲሆን በቀጣይ የስፖርት ምሁራን፣ የቀድሞ ተጫዋቾች፣ አሰልጣኞችና መገናኛ ብዙኃን አካላት የሚሳተፉበት መድረክ እንደሚኖር ጠቁመዋል። በተጨማሪም የፌዴሬሽኑ ስትራቴጂክ እቅድ ከለሳ የ2029 የአፍሪካ ዋንጫን መሰረት ባደረገ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

ለብሔራዊ ቡድኑ አሰልጣኞች ረጃጅም ኮንትራትን ለመስጠትና ውጤታማ ብሔራዊ ቡድን ለመገንባት እቅድ መኖሩን እና የሚመለከታቸው አካላት እንዲደግፉ እቅድ ተነድፎ ጥያቄ መቅረቡን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገልጸዋል። ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር ይህንን በተመለከተ መድረኮች እንደሚኖሩም ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም ብሔራዊ ቡድኑ ከመንግሥት የሚደገፍበት ሁኔታ ወደፊት ሊፈጠር እንደሚችል እምነታቸውን ተናግረዋል፡፡

ዋልያዎቹ ለጨዋታዎቹ ከጥቅምት 28 ጀምሮ ዝግጅታቸውን በአዲስ አበባ ስታድየም ሲያደርጉ የቆዩ ሲሆን፤ ትናንት ረፋድ 4፡00 ሰዓት ላይ 20 ተጫዋቾች የተካተቱበትን ልዑክ ይዘው ወደ ኮንጎ ኪንሻሳ አምርተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ካደረገቻቸው አራት ጨዋታዎች በሶስት ተሸንፋ በአንድ አቻ ስትለያይ በአንድ ነጥብ የምድቡን የመጨረሻ ደረጃ ይዛ ትገኛለች፡፡